# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 045 ጥቅምት 15 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “ታሪካዊው የኢትዮጵያና ሩሲያ የሁለትዮሽ ግንኙነት ተጠናክሮ ቀጥሏል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ታሪካዊ ቁርኝት ላይ የተመሰረተው የኢትዮጵያና ሩሲያ የሁለትዮሽ ግንኙነት ተጠናክሮ መቀጠሉን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሩሲያው አቻቸው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር ትናንት ውይይት አድርገዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ትናንት ባሰፈሩት መልዕክት፤ በሁለቱ ሀገራት ታሪካዊ ቁርኝት ላይ የተመሠረተው የሁለትዮሽ ግንኙነት እያደገ መቀጠሉንም ጠቅሰዋል።

የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ለማጠናከር እና አዳዲስ የትብብር መንገዶችን ለመፈተሽ በሚደረገው ጥረት ላይ እንደሚሠሩም ገልጸዋል።



ከዚህ በተጨማሪ መድረኩ የጋራችን በሆነው የብሪክስ መድረክ ሰፋ ያለ የኢኮኖሚ ትብብር እንድናደርግ በር ከፍቶልናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሩሲያ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢያጋጥሟትም ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ለማስጠበቅ መቻሏን አድንቀዋል። ይህም ለኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ጠንክረን ከሠራን እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከተሳተፍን ኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎች ግንኙነታችንን ማሳደግ እንችላለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በበኩላቸው፤ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችንን ያከበርንበት 125ኛ ዓመት የምስረታ በዓል የበለፀገ

“ታሪካዊው የኢትዮጵያና... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# ትኩረት የሚሻው የሥርዓተ-ምግብ እሳቤ


**መስከረም ሰይፉ**

**ዜና ትንታኔ**

በርካታ ሰዎች አሁን ላይ ታመው ወደ ሕክምና ተቋማት ከሄዱ በኋላ ‘ይሄን ምግብ አትውሰዱ፤ ይሄ ምግብ ለጤናችሁ አደጋ ነው’ ተባልን ሲሉ መስማት የተለመደ ሆኗል። የሕክምና ባለሙያዎችም ለስኳር፣ ለደም ግፊት፣ ለጨጓራና ለመሳሰሉት በሽታዎች መባባስ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ምግቦችን ለይተው ጥንቃቄ አድርጉ የሚል ምክራቸውን ይለግሳሉ።

በርካታ ኢትዮጵያዊ ስለጤናማ አመጋገብ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ስለምግብ ሲነሳ ወደ አእምሮው የሚመጣው ስጋው ፣ ዶሮው፣ ቅቤውና የመሳሰሉት ቅባት አዘል

ትኩረት የሚሻው ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




## ዲጂታል ኢኮኖሚው 1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር እንደሚያበረክት ይጠበቃል

ገጽ 2

# የዓባይ ፖለቲካ በተፋሰሱ ሀገራት መነፅር

**ማህሌት ብዙነህ**

**ዜና ትንታኔ**

የታችኞቹ የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ ሀገራት ውሃውን በብቸኝነት ለመጠቀም ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በቅኝ ግዛት ውል ስምምነት ላይ ተመርኩዘው መቆየታቸው የሚታወስ ነው።

ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ እየገነባች በምትገኘው ግድብ አማካኝነት የሚለቀቀው የውሃ መጠን ይቀንስብናል የሚል ስጋት ቢያድርባቸውም ኢትዮጵያ ግን የሚፈሰውን የውሃ መጠን ጭምር ይፋ በማድረግ ስጋታቸው ትክክል እንዳልሆነ በተደጋጋሚ አሳይታለች።




ውሃውም አሁንም ድረስ እየፈሰሰ በበቂ ሁኔታ እየደረሳቸው ይገኛል። አንዳንዴም ከባድ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት የታችኞቹ ተፋሰስ ሀገራት በጎርፍ ጭምር ሲጠቁ ላስተዋለ ስጋታቸው ልክ እንዳልነበረ መገንዘብ ይቻላል።

በአፍሪካ ቀንድ አለመረጋጋት ለማስፈን የሚሰሩ ኃይሎች የውሃውን ጥያቄ በመመርኮዝ ለተለየ ደባና ሕጋዊ ላልሆኑ አካሄዶች እጃቸውን ሲዘረጉም ይስተዋላል። ታዲያ በዓባይ ግድብ ዙሪያ በተለይም ከግብጽ በኩል እየተደረገ ያሉ እንቅስቃሴዎች መነሻቸው ምንድን ነው አላማቸውና የመጨረሻ ግባቸው ምን ያሳያል በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

የዓባይ ፖለቲካ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




## ዲጂታል ኢኮኖሚው 1 ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር እንደሚያበረክት ይጠበቃል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚ በ2021 ዓ.ም ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አንድ ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር በላይ አበርክቶ እንደሚኖረው ጂኤስኤምኤ በተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመተባበር ያወጣው ሪፖርት አመላከተ።

የተቋሙ ከሰሀራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት የፐብሊክ ፖሊሲና ኮሙኒኬሽን ከፍተኛ ዳይሬክተር ካሮሊን ምብጉዋ ትናንት ሪፖርቱን ሲያቀርቡ እንዳሉት፤ የቴሌኮም ማሻሻያና የሞባይል ቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንቶች በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ እና በሕዝብ አገልግሎቶች በመሳሰሉት ቁልፍ ዘርፎች እድገትን ያበረክታሉ።

በዚህም በ2021 ዓ.ም ከአንድ ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ሥራዎች እንደሚፈጠሩ እና ለመንግሥት 57 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ የታክስ ገቢ ያስገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ኢ.ኤ.አ. በ2023 ዘርፉ 700 ቢሊዮን ብር ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት አበርክቶ 57 ቢሊዮን ብር ከታክስ ገቢ አስገኝቷል ያሉት ከፍተኛ ዳይሬክተሯ፤ የሞባይል ኢንተርኔት ግንኙነቶች በ65 በመቶ ያደገ ሲሆን፤ የ4ጂ ሽፋን በስምንት እጥፍ መጨመሩን ጠቁመዋል።

የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነትና በቴሌኮም ገበያ ላይ ያለው ውድድር እንዲጨምር ኢትዮ ቴሌኮም እና ሳፋሪኮም ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና እንደነበራቸው አንስተዋል።

በ2021 ዓ.ም ከ50 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ከሞባይል ኢንተርኔት ጋር ይገናኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ አመላክተው፤ ይህም በ2021 ዓ.ም በግብርና ዘርፉ ላይ 140 ቢሊዮን ብር፣ በማኑፋክቸሪንግ ላይ የ114 ቢሊዮን ብር አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ያለውን የዲጂታላይዜሽን አቅም ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት አቅርቦትን ማመቻቸት፣ ፈጣን የቴሌኮም ማሻሻያ ማድረግ፣ የሞባይል ቀፎዎችን ዋጋ ተመጣጣኝነት ማሻሻል፣ የሞባይል ገንዘብ ዝውውር አገልግሎቶችን ማስፋፋት እንዲሁም የዲጂታል ክህሎትን እና የመንግሥት አገልግሎቶችን ማሳደግ የሚሉ ጉዳዮች በምክረ-ሃሳብነት ቀርበዋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ ሪፖርቱን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ ሪፖርቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚውን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለማገዝ እያከናወነች ያለው ሥራ ውጤታማነት ያሳየ ነው። በዚህም ዲጂታል ኢኮኖሚው ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ስምንት በመቶ አስተዋጽኦ ማድረጉን አመላክቷል።

ባለፉት ስድስት ዓመታት በተወሰዱ ርምጃዎች ሀገሪቱ ቀደም ሲል ከነበራት የኢንተርኔት ተደራሽነት እያደገ መምጣቱን አሳይቷል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፣ ይህም ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ላይ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ሀገሪቱን በአፍሪካ ደረጃም ተጠቃሽ የሚያደርጋት መሆኑን አንስተዋል።

ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የ2025 ስትራቴጂ ተቀርጾ በመተግበር ላይ መሆኑን ገልጸው፣ ስትራቴጂውን እውን ለማድረግም መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍና ሌሎችም ባለድርሻዎችን ትብብር ያስፈልጋል ብለዋል።

ጂኤስኤምኤ የሞባይል ስነ-ምህዳርን አንድ የሚያደርግ ዓለም አቀፍ ድርጅት ሲሆን፣ አዳዲስ ፈጠራን በመፍጠር፣ ለማዳበር እና ለመለካም የንግድ ስነ-ምህዳሮች እና የህብረተሰብ ለውጦችን ለማምጣት መሰረት አድርጎ እንደሚሠራ ተመላክቷል።

# የግብዓት አቅርቦቱና የምገባው በጀት ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርት ግብዓት አቅርቦቱና የትምህርት ቤት ምገባው በጀት ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን የምገባ ኤጀንሲው አስታወቀ፡፡ የመርሀ ግብሩ መጀመር በተማሪዎች ውጤት ላይ ለውጥ አምጥቷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የምገባ ኤጀንሲ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ምነወር ኑረዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትምህርት ቤት ምገባ በአሁኑ ወቅት ከ801ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

አጠቃላይ የግብዓት አቅርቦቱና የትምህርት ቤት ምገባው በጀት ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን ጠቁመው፤ ይንን ተሞክሮ ለማየት ከተለያዩ ሀገራት ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ አካላት ቁጥራቸው እየጨመረ ነው ብለዋል፡፡

የምገባ መርሀ ግብሩ ከሙአለ ህጻናት እስከ ስምንተኛ ክፍል መሆኑን የጠቀሱት አቶ ምነወር፤ የግብዓት አቅርቦት እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የሚሰጥ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የተማሪ ቁጥር በየጊዜው በፍጥነት እየጨመረ በመሆኑ በጀቱም እየጨመረ እንዳለ አመላክተዋል፡፡

የትምህርት ቤት ምገባ መርሀ ግብሩ ሲጀመር የተጠቃሚ ተማሪዎች ቁጥር 300 ሺህ እንደነበር አስታውሰው፤ ዛሬ ላይ ከ801 ሺህ በላይ መድረሱን አቶ



አቶ ምነወር ኑረዲን

ምነወር ገልጸዋል፡፡

ከአንድ ሚሊዮን 34ሺህ በላይ ተማሪዎች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)ና ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች ማቅረብ እንደተቻለም ተናግረዋል፡፡ ይህ በመሆኑ ከዋጋ ማሻሻያና ጭማሪው ጋር ተያይዞ በአሁኑ ወቅት የግብዓት አቅርቦቱና የምገባው በጀት ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ መድረሱን አስታውቀዋል፡፡

በትምህርት ቤት ምገባ መርሀ ግብሩ፤ ለ16ሺህ እናቶች የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህ ስራም አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ እውቅናዎች ማግኘቷን ተናግረዋል፡፡ የምገባ ማእከላቱ የበርካታ ዜጎችን ህይወት ከመደገፍ አልፎ ለተለያዩ ሀገራት ተሞክሮን የሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፤ የምገባ አገልግሎቱ በትምህርት ቤት ውስጥ መጀመር መቻሉ ዘርፈ ብዙ ውጤቶችን አስገኝቷል፡፡

በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታወቅ አብሮ የመኖርና የመደጋገፍ ባህል እንዲጠናከርና በተመሳሳይ ተማሪዎች ስለ ምግብና ስለ ትምህርት ቁሳቁስ እንዳይጨነቁ አድርጓል ብለዋል፡፡

አንድ አይነት ምግብ፣ ተመሳሳይ የደንብ ልብስና ሌሎች የመማሪያ ግብዓቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ስለሚቀርቡ በተማሪዎች መካከል ይታይ የነበረውንም ልዩነት አስቀርቷል ሲሉ ተናግረዋል።

ተማሪዎች ትምህርታቸው ላይ ብቻ ትኩረት በማድረጋቸው በውጤት ደረጃም መሻሻሎች እየመጡ ነው፡፡ ይህ ወደፊትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ነው ያሉት፡፡

# የሴቶች የመሬት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ተጠቆመ።

በሴቶች የመሬት ይዞታ መብት ላይ ያተኮረ "ለሴቷ መሬት እንቁም" (Stand For Her Land) የተሰኘ የውይይት መድረክ በትናንትናው እለት ተካሂዷል። በመድረኩ በቅርቡ የጸደቀው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ገነት ስዩም በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አዲሱ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ከውርስና ጋብቻ ጋር ተያይዞ የሚመጡ የሴቶች የመሬት አስተዳደር መብቶች ላይ ያተኮረ ነው።

በተለይም በገጠራማው የሀገሪቱ ክፍል ያለው ኋላ ቀር አመለካከት ሴቶች የመሬት ባለቤት እንዳይሆኑ፣ የውርስ መሬት እንዳይካፈሉ እንዲሁም መሬት ቢኖራቸው እንኳን ማስተዳደር እንዳይችሉ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በተሻሻለው አዋጅ በተለይም ሴቶች በውርስ የመሬት ባለቤት መሆን እንደሚችሉ በግልጽ ተቀምጧል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ወይዘሮ ገነት ገለጻ፣ ብዙ ጊዜ አዋጆች ጸድቀው አተገባበር ላይ ችግር አለ፤ ይህን አዋጅም ተግባራዊ ለማድረግ የማህበረሰቡ ባህልና ወግ መሰናክል ሊሆን ስለሚችል በትኩረት መስራት ይገባል።

ስለሆነም የሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብትን ለማረጋገጥ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በአዲሱ አዋጅ ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ 13 ነጥቦች ተካተዋል፤ አዋጁ የሴቶች መሬት ባለቤትነት እድልን የሚያጠናክር ነው ብለዋል።

አዋጁን ወደ መሬት ለማውረድ ሴቶች ላይ ትኩረት አድርገው ከሚሰሩና በማህበረሰቡ ተሰሚነት ካላቸው አካላት በተለይም ከሃይማኖት አባቶችና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በጋራ መስራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።



መሬት ሀብት ነው የሚሉት ወይዘሮ ገነት፤ ሴት ልጅ የመሬት ባለቤት ካልሆነች ሰብዓዊ መብቷን ለማስከበር ኢኮኖሚዋ ጥቅሞቿን ለማሳደግ ይረዳታል ሲሉ አንስተዋል።

በሀቢታት ፎር ሂውማኒቲ ኢትዮጵያ የስታንድ ፎር ኸር ላንድ ፕሮጀክት ማናጀር የሆኑት ወይዘሮ ናርዶስ አሸቱ በበኩላቸው፣ የውይይት መድረኩ ሴቶች በመሬት ይዞታቸው ላይ የመወሰንና የመጠቀም መብት ላይ ያተኮረ መሆኑን ተናግረዋል።

አላማውም የተሻሻለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ለሴቶች ምን አይነት እድል ይዞ እንደመጣ ግንዛቤ መፍጠር ነው ብለዋል።

የነበረው አዋጅ ሴቶች ላይ ትኩረት ያደረገ አልነበረም የሚሉት ወ/ሮ ናርዶስ፣ አዲሱ አዋጅ ግን የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት መብትን በግልጽ ያስቀመጠ መሆኑን ገልጸዋል።

በአዋጁ መጀመሪያ ላይ ሴቶች የመሬት፣የንብረት መጠቀምና የማስተዳደር መብትን ለማስጠበቅ የሚረዱ አንቀጾች በዝርዝር መቀመጣቸውን ጠቁመው፣ ይህም ከቀድሞው አዋጅ ጋር ሲነጻጸር ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግና የተሻለ መሆኑን አስረድተዋል።

ሕግ ተርጓሚና አስፈጻሚ አካላትም አዲሱ አዋጅ ትኩረት በሰጠው የሴቶች ጉዳይ ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ የሚያግዝ መሆኑንም ተናግረዋል።

በስታንድ ፎር ኸር ላንድ ፕሮጀክት በተደረገ ጥናት ሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብታቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሲነጠቁ መጠየቅ እንዳለባቸው ግንዛቤው እንደሌላቸውና ሕጉንም አውቀው ወደ ፍርድ በሚሄዱበት ወቅት አፈጻጸም ላይ ክፍተት እንዳለ ማወቅ ተችሏል ብለዋል።

በሌላ በኩል ባህላዊ አሰራሮች ለወንዶች ያደሉ መሆናቸው ሴቶች በመሬት ባለቤትነት ዙሪያ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ማድረጉን ጥናቱ ማመላከቱን ገልጸዋል።

ዜና

# አማኑኤል የአዕምሮ ሆስፒታል በቀን 600 ሕሙማንን እያስተናገደ ነው

## - የአዕምሮ ሕክምና በሁሉም የጤና ተቋማት ሊቀርብ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በቀን 600 ሕሙማንን እያስተናገደ መሆኑን አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አስታወቀ። የአዕምሮ ሕክምና አገልግሎት በሁሉም የጤና ተቋማት ማቅረብ እንደሚገባ ተመላክቷል።

የአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሜዲካል ዳይሬክተር ረዳት የሆኑት አቶ አያሌው አባተ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በሀገር አቀፍ ደረጃ የአዕምሮ ሕክምናን ለረዥም ዓመታት በብቸኝነት የተመላላሽ፣ አስተኝቶ ሕክምናና በድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በቀን ከ500 እስከ 600 ሕሙማንን እያስተናገደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሀገሪቱ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና መስጫ ተቋማትን ጨምሮ በሁሉም የጤና ተቋማት የአእምሮ ሕክምና መሰጠት ይኖርበታል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ሁሉም ክልሎች እራሳቸውን የቻሉ ትላልቅ የአዕምሮ ሕክምና መስጫ ማዕከላት ሊኖሩ እንደሚገባም አቶ አያሌው ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች ጋር ሳያካትት የሥነ-አዕምሮ ሕክምናን በብቸኝነትት የሚሰጥ የጤና ማዕከል መሆኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ጫና እየፈጠረ መሆኑን አንስተዋል። ከ120 ሚሊዮን በላይ ለሆነ ሕዝብ የሚያገለግል ብቸኛ የመንግሥት ተቋም መሆኑ ጫናውን እንደሚያሳይ ጠቁመዋል።

ሆስፒታሉ ረዥም ዓመታትን ያስቆጠረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አገልግሎቱ በሚፈለገው መጠን እንዳልዘመነ አስታውቀው ፤ በግቢው ውስጥ የመሰረተ ልማት፣ በቂ የታካሚዎች አልጋ እጥረት እና የሥነ-አዕምሮ ባለሙያዎችና የግብዓት እጥረት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

ባለፉት ሶስት ዓመታት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሕክምናውን ፈልገው የሚመጡ ታካሚዎች በተለያዩ አካባቢዎች በተከሰቱ አለመረጋጋቶች ሳቢያ መምጣት ባለመቻላቸው የተገልጋይ ቁጥሩ ቀንሶ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ላይ በቂ የሕክምና መስጫ ቦታ ባለመኖሩ በአገልግሎቱ ላይ ከፍተኛ መጨናነቅ አለ ብለዋል፡፡

በሆስፒታሉ ሕክምና የጀመሩትን በቅብብሎሽ ወደሚቀርባቸው ጤና ተቋማት በመላክ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ እየተሰራ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ጥራት ያለውን አዕምሮ ሕክምና ተደራሽ በማድረግ ብሎም በሆስፒታሉ ያለውን ጫና በመጠኑ የሚቀንስ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የአዕምሮ ሕክምና አገልግሎቱን ለማስፋት በሁሉም የጤና ተቋማት የአዕምሮ ሕክምና መሰጠት አለበት የሚል ስትራቴጂ መቀመጡን አስታውቀዋል።

የተቀመጠውን ስትራቴጂ ሁሉም የጤና ተቋማት በመተግበር የሥነ-አዕምሮ ባለሙያዎች እንዲቀጥሩ እና ቀላል የአእምሮ ህክምና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የህብረተሰቡን የአዕምሮ ጤና የመጠበቅ አገልግሎት በአንድ ሆስፒታል ብቻ የሚሰራ ባለመሆኑ በቂ በጀትና ባለሙያዎችን በማሰማራትና ተቋሙን ማበረታታት በተለይም አምራች ዜጋውን እያጠቃ ለሚገኘው የአዕምሮ ህመም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ብለዋል፡፡

አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በቀጣይ በሥነ-አዕምሮ የልህቀት ማዕከል የመሆን እቅድን በመያዝ እየሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ ከአዕምሮ ሕክምና በተጨማሪ ለታካሚዎች የውስጥ ደዌ፣ የማዋለድና ሌሎች ተጨማሪ የጤና አገልግሎቶችን በማካተት ሕክምና ለመስጠት ማቀዱን አስታውቀዋል፡፡

በአዕምሮ ህመም ዙሪያ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን የጤና ባለሙያውም ጭምር የተሳሳተ እሳቤ እንዳላቸው ጠቅሰው፤ የአዕምሮ ህመም ታክሞ መዳን የሚችል በመሆኑ ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ሊኖረውና ወደሕምክና ተቋማት መሄድ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

# ዘላቂ ኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ የሰው ሀብት ልማት ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ የሰው ሀብት ልማት ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩትና የአፍሪካ የኢኮኖሚ ምርምር ኮንሰርቲየም "የሰው ሀብት ልማት በኢትዮጵያ" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት የፖሊሲ ውይይት አካሂደዋል። በተጨማሪ ተቋማቱ በጋራ ለመሥራት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር አቶ ፍቃዱ ጻጋ በውይይቱ ላይ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ የሰው ሀብት ልማት ላይ በትኩረት ሊሠራ ይገባል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ፖሊሲ ለሚያወጡ የመንግሥት አካላት ምርምርና ሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ መሰረት ያደረገ ጥናት በማድረግ ግብዓት እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ ለፖሊሲ የሚጠቅሙ ሰነዶችን እንደሚያዘጋጅ አስረድተዋል። ተቋሙ የፖሊሲ ሰነዶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንደሚያቀርብ ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የሰው ሀብት ልማት ለኢኮኖሚ እድገት ጠቃሚ ነው ያሉት አቶ ፍቃዱ፤ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ የሰው ኃይል ልማት ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

ምርምሮችን ሴክተር መስሪያ ቤቶች እንዲጠቀሙበት እንደሚደረግም ጠቁመው፤ በውይይቱ ላይም የትምህርት ጥራት ችግር ያልተሻገረችው ችግር እንደመሆኑ ከለውጡ ወዲህ በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ቢሆንም የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንደሚጠይቅ አመላክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የሰው ሀብት ልማት ለዘመናት የቆዩ ችግሮች እንዳሉበት በመግለጽ፤ የትምህርት ተቋማትን ተደራሽ በማድረግ በኩል የተሠራ ቢሆንም ጥራት ላይ ግን በሚፈለገው ልክ አለመሠራቱን አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያለው ትልቁ ሀብት የሰው ኃይል ቢሆንም ያለው እውቀት ደግሞ በቂ አለመሆኑን ጠቅሰው፤ በትምህርት ተደራሽነትና ጥራት ላይ የተጀመሩ ሥራዎች አጠናክሮ በማስቀጠል የሚፈለገውን የሰው ኃይል ልማት ማሳካት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

የአፍሪካ ኢኮኖሚ ምርምር ኮንሰርቲየም የምርምር ዳይሬክተር አቢ ከድር (ፕ/ር) በበኩላቸው፤ በትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ከተቻለ ውጤታማ የሰው ኃይል ልማትን ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

የትምህርት ጥራት ለአንድ ሀገር የሰው ኃይል ልማት ወሳኝ ነው ያሉት ፕሮፌሰር አቢ፤ በውይይቱም በትምህርት ጥራትና በተማሪዎች ምገባ መርሀ ግብር ላይ ሰፊ ውይይት መደረጉን አንስተዋል።

ጥናቱን ተከትሎ የቀረቡት የፖሊሲ ምክረ ሃሳቦች የተማሪዎች ምገባ መርሀ ግብሩ በሁሉም የክልልና የከተማ አስተዳደር አካባቢዎች ላይ ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ ማመላከቱን ጠቅሰው፤ በቀጣይ በትምህርት ጥራትና በሰው አቅም ግንባታ ላይ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ የሚያመላክት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የመግባቢያ ስምምነቱ ተቋማቱ ቀደም ሲል ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚያስችል ገልጸው፤ የሰው ኃይል ልማት ፕሮጀክትን ጨምሮ ሌሎች ተግባራትንም በጋራ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑን አስታውቀዋል።

# በመዲናዋ የአካባቢ ብክለት ባስከተሉ 701 ተቋማት ላይ ርምጃ ተወሰደ

## - ፎቅ ላይ ጭፈራ ቤት ከፍተው የድምጽ ብክለት የሚያስከትሉ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በ2017 በጀት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የአካባቢ ብክለት ባስከተሉ 701 ተቋማት ላይ ርምጃ መውሰዱን የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡ ከፍ ባለ ቦታዎች በተለይም ፎቅ ላይ ጭፈራ ቤት ከፍተው የድምጽ ብክለት የሚያስከትሉ ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንደሚገባ ባለስልጣኑ አሳሰቧል።

ባለስልጣኑ የ2017 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት እቅድ አፈጻጸም መድረክ አካሂዷል፤ በተጨማሪ "ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ" በሚል መሪ ሃሳብ ላለፉት ስድስት ወራት ሲያካሂድ የቆየውን አካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ የማጠቃለያ ሪፖርት ትናንት አቅርቧል።

የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዲዳ ድሪባ እንዳስታወቁት፤ በመዲናዋ በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 701 የአካባቢ ብክለት ባስከተሉ ተቋማት ላይ ርምጃ ተወስዷል፡፡

የአካባቢ ብክለት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ከማጠናከር አንጻር ባለፉት ሦስት ወራት በሁለት ሺህ 316 ተቋማት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች መሰራቱን አስታውሰዋል።

በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ሦስት ወራት 190 በላይ የአካባቢ ብክለት ይወገድልኝ አቤቱታዎች ከህብረተሰቡ መቅረባቸውን ጠቁመው፤ ከእነዚህም ውስጥ አብዛኞቹ የድምጽ ብክለት መሆናቸውን አቶ ዲዳ ተናግረዋል፡፡

በተለይም ከከፍታ ላይ የሚሰማ ድምጽ ብዙ ቦታ የሚረብሽ በመሆኑ ፎቆች ላይ ጭፈራ ቤት የሚከፍቱና የተለያዩ የድምጽ ብክለቶች የሚያስከትሉ ተቋማት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡

የድምጽ ብክለትን ለመከላከልም አራት የባለሙያ ቡድኖች ተዋቅረው በሦስት ቀናት ውስጥ ከ200 በላይ ቤቶች ላይ የቁጥጥር ስራ አከናውነው ከሚጠበቀው መስፈርት በላይ የድምጽ ብክለት ያስከተሉት ተለይተው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የአካባቢ ብክለት ለመከላከል፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቋቋም የሚችልና ስነ-ምህዳሩ የተጠበቀ ከተማ ለመገንባት በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ አቶ ዲዳ ገልጸዋል።

በስድስቱ ወራት የተከናወኑት የአካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ ስራዎች ህብረተሰቡ ስለ አካባቢ ብክለት ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ጠቁመዋል።

በስድስት ወራት የተካሄደው የአካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ መደበኛ ሥራ ሆኖ ይቀጥላል ያሉት አቶ ዲዳ፤ በቀጣይም የአካባቢ ብክለት የመከላከል ሥራው በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ዲዳ ገለጻ፤ በከተማው እየተከናወኑ ያሉ የኮሪደር ልማትና የወንዝ ዳር ፕሮጀክቶች የመዲናዋን የአካባቢ ብክለት ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የብሪክስ ተሳትፏችን ግቡ የሀገር እና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ማጎልበት ነው

ብራዚል፣ ሩስያ፣ ሕንድ፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካን በጋራ ያሰባሰበው እና በእንግሊዘኛው ምኅጻረ ቃል (BRICS/ ብሪክስ) ተብሎ የሚጠራውን ህብረት፤ በአንድ ጎራ ተሰልፎ ዓለምን ወደ አንድ ቦይ እንድትፈስስ አማራጭ ያሳጣውን የምዕራቡ ዓለም ስብስብን ተገዳዳሪ ሆኖ የቀረበ ብቻ ሳይሆን፤ የዓለምን ሚዛን የማስጠበቅ ተስፋ የተጣለበት ስብስብ ነው።

ይሄ ህብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅምና ተጽዕኖ ፈጣሪነቱን እያሳደገ የመጣ፤ በብዙ ሀገራት ዘንድም የአባልነት ጥያቄ እየጎረፈለት ያለ ሲሆን፤ ስብስቡን ለመቀላቀል ከቀረቡ በርካታ ጥያቄዎች መካከልም ለመጀመሪያ ጊዜ ስድስት ሀገራትን (ኢትዮጵያ፣ የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ አርጀንቲና፣ ኢራን እና ግብጽ) በአዲስ አባልነት ተቀብሎ የኅብረቱን አባላት ቁጥር ወደ አስር ማድረስ ችሏል።

ኢትዮጵያም በብራዚል፣ ሩስያ፣ ህንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ በተመሰረተው የብሪክስ አባል ከሆነች ወራቶች ተቆጥረዋል። ከዓለም 47 ከመቶ የሚጠጋውን ሕዝብ ባቀፈው፤ ከዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ 30 በመቶ ድርሻ ባለው፤ በተናጥልም የባለግዙፍ ኢኮኖሚ እና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገራት ስብስብ በሆነው ኅብረት ውስጥ አባል ሆና መገኘቷም በብዙ መልኩ ተጠቃሚ የሚያደርጋት ነው።

በተለይም እንደ ሀገር ለጀመርነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ሀገራዊ ጉዞ መሳካት የሚያስፈልገውን ዘርፈ ብዙ ድጋፍ (ቴክኖሎጂ፣ ገንዘብ፣ የእውቀትና እና ሌሎችም አዎንታዊ ድጋፎች) ለማግኘት ትልቅ እድል የሚሰጣት ነው። በሁለትዮሽ በተለይም በባለብዙ ወገን የትብብር ሂደት ላይ የዲፕሎማሲ እና ሌሎች አቅሞችን በመፍጠርም በዓለም ኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሚኖረንን ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ተሰሚነት ከፍ የሚያደርግ ነው።

በዋናነት መሠረተ ልማት እና ቀጣይነት ያላቸው የልማት ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ በብሪክስ አባል ሀገራት ከተመሰረተው “ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ“ እንደ ሀገር ስትራቴጂክ ተጠቃሚነትን ይሰጣል። ያለብንን የውጭ ምንዛሪ ችግር ለመቅረፍም አማራጭ ይሆናል፤ አማራጭ የገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓትንም ያሰፋል።

ከዚህም ባለፈ በፍጥነት እያደገ ላለው የሀገራችን ኢኮኖሚ፤ በኢንቨስትመንት፣ በኢኮኖሚ ትብብርና በንግድ ወሳኝ የሆኑ አዳዲስ ዕድሎች ይዞ ይመጣል። ሀገሪቱ ያሏትን የተፈጥሮ ሀብቶች አልምታ ለመጠቀም የሚያስፈልጋትን ቴክኖሎጂ እና ሀብት በማሟላት ሂደትም አበርክቶ ከፍያለ አለው።

በተለይም በኅብረቱ የተመሰረተው ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ ፣ እንደ ሀገር የታቀዱ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ ለማድረግ ያለብንን የሀብት ውስንነት ለመሻገር በምናደርጋቸው ጥረቶች ውስጥ የሚያጋጥሙንን አላስፈላጊ የፖለቲካ ጫናዎች በቀላሉ ተሻግረን ፕሮጀክቶቻችንን ማስፈጸም የምንችልበትን የተሻለ እድል የሚፈጥር ነው።

የሀገሪቱ የውጪ ፖሊሲ የሀገር እና የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም እና አካታችነትን መርሑ ያደረገ ነው። የብሪክስ አባልነቷም ከዚህ እውነታ የተቀዳ ሲሆን፤ ከሁሉም በላይ ለሀገር እና ለሕዝብ ዘላቂ ስትራቴጂክ ጥቅም ማስገኘትን ያስቀደመ ነው። ለዚህ ጉዞው መሳካት ደግሞ ወዳጆችን በማፍራት የጋራ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን እውን የማድረግ ግብን ያስቀመጠ ነው።

እንደ ሀገር ከኋላቀርነት እና ከድህነት ፈጥነን ለመውጣት የምናደርገው ጥረት፤ ተለዋዋጭ በሆነው አሁናዊ ዓለም ያሉትን አማራጮች በሙሉ መጠቀምን የሚጠይቅ ነው። ከዚህ አንጻር መንግሥት ሀገሪቱን የብሪክስ አባል ለማድረግ የሄደበት መንገድ ጥልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ከመሆን ባለፈ፤ ነገዎቻችንን ብሩህ ለማድረግ ለጀመርነው አዲስ የታሪክ ጉዞም ተጨማሪ አቅም ነው።

ለዚህም በአፍሪካ ብሎም በዓለም በመንገደኞችና በጭነት አገልግሎት በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ እንደ ሀገርም ለጎረቤት ሀገራት ጭምር በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርበው የታዳሽ ኃይል፤ ወጣት፣ የተማረና በቀላሉ ሊሰለጥን የሚችል የሰው ኃይል እና ሌሎችም አቅሞቿ ሀገሪቱን ለኢንቨስትመንትና ንግድ ሳቢ ያደርጋታል።

ለዚህ ተደማሪ አቅም በሚሆን መልኩም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለቢዝነስ ምቹ ለማድረግ ከቅርብ ዓመታት ጀምሮ የተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች፤ ቴሌኮሙኒኬሽንና ፋይናንስን ጨምሮ ቁልፍ ሴክተሮች ላይ የተደረጉ ለውጦችና ማሻሻያዎች፤ በቅርቡም የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲመራ ለማድረግ የተወሰደው እርምጃ እና ሌሎችም ተግባራት ሀገሪቱን ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ምቹ የሚያደርጋት ነው።

እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች የአባል ሀገራቱ ባለሀብቶች እንደ እድል ወስደው በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በታዳሽ ኃይል፣ በማዕድንና በቱሪዝም መስኮች ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያነቃቃ ነው። ከዚህም ባለፈ ብዙዎቹ የብሪክስ አባል ሀገራት በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚ ትልቅ አቅም የፈጠሩ መሆናቸው፤ ኢትዮጵያ ኅብረቱን መቀላቀሏ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ትልቅ እድል ይፈጥርላታል።

በመሆኑም በእነዚህና በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ዛሬ ላይ እንደ አንድ የብሪክስ አባል ሀገር በህብረቱ ውስጥ ያለን ተሳትፎ፣ ጅማሬውም ሆነ ፍጻሜው የሀገር እና የሕዝብን ተጠቃሚነት እውን ማድረግ እንደመሆኑም፤ ለጀመርነው በልማት ድህነትን ታሪክ የማድረግ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ተጨማሪ አቅም የመፍጠር ስትራቴጂክ ጉዞ ነው።

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጉዞ ወደ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025

ክብረአብ

አሁን ባለንበት ዘመን ያለ ቴክኖሎጂ ህይወት ፈታኝ ነው። ከግለሰብም አልፎ ሀገራትም ያለ ቴክኖሎጂ ያሰቡትን እድገት እና ብልጽግና ማረጋገጥ አይችሉም።

ለዚህ ነው ከበለጸጉት እስከታዳጊ ሀገራት ድረስ ቴክኖሎጂን ለማልማትና ለመጠቀም ትኩረት ሰጥተው በመስራት ላይ የሚገኙት።

ኢትዮጵያ ለቴክኖሎጂ ትኩረት ከሰጡ ሀገራት አንዷ ነች። ስትራቴጂክ የእድገት ዘርፎች በሚል በፖሊሲ ደረጃ ልዩ ትኩረት ከሰጠቻቸው ዘርፎች ውስጥ ቴክኖሎጂን አንዱ የትኩረት አቅጣጫ አድርጋ መውሰዷም ለዚህ ነው። ዲጂታል ኢትዮጵያ የሚለው መርሃ ግብር በመቅረጽም በ2025 በሁሉም ዘርፍ ቴክኖሎጂ መሪ ሆኖ እንዲወጣ እየተሰራ ነው።

**የመንግሥት አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ስመተግበር የሚያስችለው ስትራቴጂ አንዱ ነው**

በርግጥ ቴክኖሎጂ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃር የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። የአጠቃቀም ሂደቱን ብንመለከት ደግሞ እንደ ዘርፎቹ አይነት ጥቅም ላይ የሚውልበት መንገድም ይለያያል፣ የሚጠቀምባቸው መሳሪያዎችም እንዲሁ እንደ አገልግሎቱ አይነትና ስፋት ይለያያሉ። እንደ ኢትዮጵያ ላሉና በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ ፋይዳው ከምንለው በላይ ትልቅ ነው።

ኢትዮጵያም የዲጂታል ዓለምን ለመቀላቀል የሚያስችላትን ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ተቀብላ ዲጂታላይዜሽን ለማስፋፋት የሚያስችሉ ሥራዎችን እየሰራች ነው። አሁን ላይ ሥራው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በበላይነት እየመራው ይገኛል።

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መረጃ እንደሚያመላክተው፤ ዲጂታላይዜሽንን በማስፋፋት ረገድ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጎ በርካታ ሥራዎች መስራት ተችሏል። በዚህም ከ526 በላይ የሆኑ የመንግሥት አገልግሎቶች በኤሌክትሮኒክስ መንገድ እንዲፈጸሙ፤ የክፍያ ሥርዓቶችም በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ሥርዓት እንዲሆኑ እና የተለያዩ መተግበሪያዎች እንዲለሙ ተደርጓል።

በዲጂታል ቴክኖሎጂው በኩል የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ሊያሰፉ የሚችሉ ሥራዎችን መስራት ተችሏል። ባለፈው ወር መጨረሻም የዲጂታል ሳምንት በማካሄድ በዲጂታል ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎችን ኅብረተሰቡ እንዲረዳቸውና እንዲገነዘባቸው ማድረግ የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተሰርተዋል ።

ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ከተሰሩ ሥራዎች አንዱ ፤ የመንግሥት አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ለመተግበር የሚያስችለው ስትራቴጂ አንዱ ነው። ስትራቴጂው በቀጣይ አምስት ዓመት የኤሌክትሮኒክስ ዘርፉ የሚመራበትን አቅጣጫ ለማመላከት ታልሞ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ስትራቴጂውን አጠናቅቆ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችል ዘንድ የመጨረሻ ግብዓት ማሰባሰብ ተችሏል።

ስትራቴጂው በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል ነው፤ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የመተግበሪያ ልማት፣ የሰው ኃይል ልማት፣ አወቃቀር እና በጀትን አካትቶ የያዘ መሆኑ ተገልጿል። ስትራቴጂው ከ2016 እስከ 2020 ዓ.ም ተግባር ላይ የሚውል መሆኑም ተመላክቷል።

እንደ ሀገር በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂና በአዲስ የፈጠራ ሥራ መታገዝ የግድ ሆኗል፤ ያለቴክኖሎጂ ያለሙበት መድረስ ከባድ እየሆነ መጥቷል። ከእነዚህ ዘመን አፍራሽ የቴክኖሎጂ ዘርፎች መካከል አርተፊሻል ኢንተለጀንስ ወይም የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቀዳሚውን ስፍራ እየያዘ መጥቷል።

ሰው ሰራሽ አስተውሎት በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ዘርፎች ምርታማነትን ለመጨመር እንዲሁም አምራች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ለማስተሳሰር ቁልፍ ቴክኖሎጂ ነው። ሰው ሰራሽ አስተውሎት/artificial intelligence/ በአሁኑ ወቅት በትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በጤና፣በደህንነት እና በግብርና ዘርፎች ምርታማነትን እና ቅልጥፍናን ለመጨመር ቁልፍ ቴክኖሎጂ ሆኖ እያገለገለ ነው።

በኢኮኖሚው ረገድም መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ የዚህ ቴክኖሎጂ ድርሻ በዓለም ገበያ 350 ቢሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል። ይህ ቴክኖሎጂ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን እና ህይወታችንም ሰፊ ድርሻ እየያዘ መጥቷል። ያደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ቴክኖሎጂው በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች እንደ አስፈላጊነቱ እየተጠቀሙበት ችግሮቻቸውን እየፈቱ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች። የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና፣ የጤና፣ የደህንነት፣ እና መሰል ዘርፎችን አቅም ለማሳደግ እየተሰራ ይገኛል።

ሰው ሰራሽ አስተውሎት ማሽን ወይም ኮምፒዩተር የሰው ልጆችን ተክቶ ማመዛዘን፣ መማር፣ ማቀድ እና ፈጠራዎችን ማከናወን እንዲችል የሚያደርግ ነው። በዚህ ሁኔታ ማሽኖቹ አካባቢያቸውን እንዲገነዘቡ፣ የተገነዘቡትን እንዲተነትኑ ፣ ችግሮችን እንዲፈቱ እና አንድ የተወሰነ ግብ እንዲደርሱ ለማድረግ ያስችላቸዋል።

ይህም በተለይ የሰዎችን ንክኪ በመቀነስ ለምርት መጨመር፣ የጊዜ አጠቃቀምን ለማሻሻል፣ ብልሹ አሰራሮችን ለማስወገድ እና ውስብስብ ስራዎችን ያለ ከፍተኛ ወጪ ለመፈፀም ያስችላል። ከጊዜ አንፃርም ያለማቋረጥ እና ያለ ምንም እረፍት ይሰራል ይህም የህብረተሰብን ኑሮ የሀገርን ዕድገት እንደሚያቀላጥፍ ያስረዳል።

በ2030፣ 50 በመቶ የሚሆነው ስራ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እንደሚተካ ይጠበቃል። በ2020 አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኮቪድ 19 ለማጥናት ጥቅም ላይ ውሏል። 2030- አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ለዓለም ኢኮኖሚ 15.7 ቢሊዮን ዶላር አስተዋጽኦ እንደሚያደርግም ይጠበቃል፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጤና አገልግሎት የጥራት እና ተደራሽነት ውስንነት አለበት። በታዳጊ ሀገራት ደግሞ ችግሩ ሰፊ ነው። በመሆኑም ኢትዮጵያም ይህንን ችግር ለመቅረፍና የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ለማዋል መረባረብ የግድ እንደሚሉት እሙን ነው።

ይህ ቴክኖሎጂ በሁሉም ዘርፎች ሰፊ ተግባራት ያሉት በመሆኑ ከቅንጦት ይልቅ ለህብረተሰብ ያለው አስፈላጊነት ግንዛቤ እያገኘ መጥቷል፤ ቴክኖሎጂው በተለይ በአፍሪካ ከባድ በሽታዎችን ለማስወገድ፣ የጤና እንክብካቤን እና ትምህርትን ለማሻሻል፣ ድህነትን ለመቀነስ እና በአህጉሪቱ ለሚታየው የምግብ እጥረት የላቁ መፍትሔዎችን ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይገባል።

የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ ለቴክኖሎጂ የሰጠው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ዓለም ካለችበት ነበራዊ ሁኔታ አንፃርና ሌሎች ሀገራት በዘርፉ ከደረሱበት ልህቀት አኳያ አሁንም ብዙ መሥራት ይጠበቃል። በተለይ የመንግሥት ተቋማት ላይ ያለው የቴክኖሎጂ ፍላጐት አሁንም ገና በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ መረባረብ ተገቢና አስፈላጊ ነው።

ተቋማት ቴክኖሎጂን ተጠቅመው የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያዘምኑ በፖሊሲ ደረጃ አቅጣጫዎች ቢኖሩም በተግባራዊነቱ ላይ አሁንም ክፍተት ስለመኖሩ በተጨባጭ የሚስተዋል ነው። ተቋማት ከለመዱት አሰራር ተላቀው የተሻለ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ አሁንም በትኩረት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፤ ለዚህ ደግሞ እራሳቸውን በሁለንተናዊ መልኩ ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

# የዓባይ ፖለቲካ በተፋሰሱ ሀገራት…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት /ኢዴኅ/ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ በርሔ፤ ግብጽ የዓባይ ወንዝ የውሃ ድርሻዬ ይጎልብኛል ከሚል መሰረት ከሌለው ስጋት በመነሳት በኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ ሴራዎችን እንደምትሸርብ ያነሳሉ።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ሆን ተብሎ በመከፋፈል የውስጥ አለመረጋጋት ለመፍጠርና የውስጥ ችግሮቻችንን ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዳንፈታ እያደረገች ያለችው ጥረት ለኢትዮጵያውያን አዲስ አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡

ኢትዮጵያ በመልክዓ ምድሯ የተገኘውን የውሃ ሃብት እንዳትጠቀም የሚከለክላት ዓለም አቀፍ ሕግ አለመኖሩን ጠቁመው፤ የዓባይ ወንዝ ሀብትን እንዳንጠቀም ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፤እያደረገችም ነው ይላሉ፡፡

በዚህም እንደእብድ ውሻ በየአቅጣጫው ተጽእኖ ለመፍጠር በሱዳን፣ በኤርትራ ፣ በደቡብ ሱዳን አሁን ደግሞ በሱማሊያ በኩል የተለያዩ ጥረቶችን በማድረግና ችግር ለመፍጠር ጥረት እያደረገች ቢሆንም የሱማሊያ ሕዝብ ከፍተኛ ጥላቻውን ሲያሳይ መቆየቱን አንስተዋል።

በአንድ አህጉር እንደመኖራችን እንደ ጉርብትናችን ተከባብረንና ተሳስበን፤ ችግሮች ቢኖሩም ተወያይቶ መፍታት ሲቻል ወደማስፈራራትና ደባ ውስጥ የመግባት አዝማሚያ መኖሩ የዓባይ ወንዝ ተጠቃሚነት ላይ ያለባቸውን ስጋት ያሳያል ይላሉ። ይህ አካሄድ ትክክለኛው መንገድ ባለመሆኑ መተባበር ላይ የተመሰረተ አካሄድን መከተል እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

ህዳሴ ግድብን ሱዳን እና ግብጽን በማይጎዳ መልኩ በጋራ እንጠቀማለን ተብሎ እንደሚታሰበው ሁሉ



ዲፕሎማሲ ጥረትና ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ ስራው ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ነው ያመላከቱት፡፡

መንግሥት እውቀትን መሰረት ያደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችና መግባባቶች ለመፍጠር የሚያከናውናቸው ስራዎች የሚደገፉ መሆኑን ጠቅሰው፤ የውሃ ዲፕሎማሲው በናይል የትብብር ማሕቀፍ የታገዘበት መንገድም አስፈላጊ መሆኑን ነው ያነሱት።

አቶ ገብሩ እንደሚገልጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወታደራዊ አቅም እና በሀገር ፍቅር ምንም ያህል ችግሮች ቢኖሩበትም ቀፎው እንደተነካበት የንብ መንጋ በጋራ ለሀገር ሉአላዊነትና አንድነት የሚቆም ቆራጥ ሕዝብ መሆኑ ከዓድዋ ጀምሮ ያሳየ በመሆኑ ችግሮች ቢመጡ እንኳን ተባብሮ የማለፍ ልምድም አለው።

በተለይም ግብጽ ኢትዮጵያን በዓባይ ግድብና የባህር በር እንዳታገኝ የምታደርገው ጥረት ብሎም ሱማሊ ላንድን በማስፈራራትና የጋራ ጠላትን ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት የማይሳካ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

አቶ ገብሩ እንደሚሉት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሀገርን ህልውና መሰረት አድርገው የተቋቋሙ በመሆኑ ከመነጣጠል ይልቅ በጋራ ከመንግሥት ጎን በመቆም የዓባይ ዲፕሎማሲያዊ ስራን ማገናዘብ ለሀገር ዘብ የመቆም ልምድን ሊያዳብሩ ይገባል፤

የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ /ኢሶዴፓ/ አባል አቶ ሉምባ ደምሴ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ እና ግብጽ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ረዥም ዓመታትን የፈጀ ቢሆንም በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አይደለም ይላሉ፡፡

በተለይም ግብጽ የዓባይን ውሃ ጥቅም የጋራ ለማድረግ ከተፋሰሱ ሀገራት አዲስ ስምምነት የማፈንገጥ ባህሪ እያሣየች መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ለጋራ ጥቅምና ሰላም እጇን ዘርግታ ጥያቄ ብታቀርብም ግብጽ ብዙውን ጊዜ ከራሷ ጥቅም ጋር እንጂ የጋራ ጥቅም እሳቤ እንደማታይ ያስረዳሉ።

መንግሥት የሰላም እጁን እየዘረጋ ጥረት ቢያደርግም በምላሹ ግን እንደግብጽ ያሉ ሀገራት የኢትዮጵያን ሉአላዊነትን ለመጋፋትና የተፈጥሮ ሀብታችንን እንዳንጠቀም የሚሰሩትን ስራ እግር በእግር ተከታትሎ ማምከን እንደሚገባም ይጠቁማሉ።

ከመንግሥት በተጨማሪም ፖለቲካ ፓርቲዎች በሀገር ጉዳይ የሚወጡት ሚና ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ሉምባ ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ አላማ ልዩነት ቢኖራቸውም ውድድርንና ሰላምን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው ከሀገር አቀፍ እንቅስቃሴና ከሀገር ጥቅም ጋር የተያያዘ ስራ ማከናወን አለባቸው ይላሉ።

በመሆኑም ፓርቲዎች በዲፕሎማሲው፣ የውስጥ አንድነትን በማጠናከር እንዲሁም ከሴረኞች ጋር ባለመተባበር ለሀገራቸው ያላቸውን አበርክቶ ከፍ ማድረግ እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ከየትኛውም ተላላኪ አካላት ነጻ በመሆን በሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ያለማዳላት በጋራ የሚሰሩ መሆናቸውን በተግባር ማሳየት እንደሚገባቸው ይጠቁማሉ።

ሁሉም ሊኖር የሚችለው ሀገር ስትኖር ነውና በዓባይ የውሃ ፖለቲካ ላይ ተንተርሶ የሚመጣን እኩይ ተግባር ለመመከት ቴክኖሎጂን፣ አንድነትን፣ ዕውቀትና ሙሉ አቅም ተጠቅሞ መስራት እንደሚገባም የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊዎቹ ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

# ትኩረት የሚሻው የሥርዓተ-ምግብ…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መብሎች ናቸው። አትክልትና ፍራፍሬዎች ደግሞ የኢኮኖሚ አቅም ያነሰው ብቻ የሚመገባቸው አድርጎ የመውሰድ ችግር ይስተዋላል።

"ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል" የሚሉ ብሂሎች አትክልት አላስፈላጊ አድርጎ የመውሰድ ለጥንካሬና ለጉልበታማነት ደግሞ ስጋና ሌሎቹን ምግቦች ተመራጭ አድርጎ የመውሰድ የተዛባ አመለካከትን የሚያሰርፁ ናቸው።

አትክልትና ፍራፍሬን የችግር ጊዜ መውጫ ብቻ አድርጎ የመመልከት ችግሩ ለጤናማ አመጋገብ ተመራጭ አለመሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለመሆኑ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት ምንድነው? ጤናማ የሚባለው የአመጋገብ ስርአት የትኛው ነው ?ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓትንስ አለመከተል ምን ያስከትላል? ሲል የጤና ባለሙያዎችን አነጋግሯል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የሥርዓተ-ምግብ ማስተባበሪያ ክፍል የመከላከል ተኮር ሥርዓተ ምግብ ዴስክ ኃላፊ ቅድስት ወልደሰንበት እንደሚሉት፤ በሀገሪቱ ስለ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት ያለው ግንዛቤ አነስተኛና እንደቅንጦት የሚወሰድ ነው።

ነገር ግን ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓትን ባለመከተል የተነሳ ህጻናት በመቀንጨር አዋቂዎች ደግሞ በተለያዩ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እየተጠቁ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

በቅርቡ ጤና ሚኒስቴርና ዩኒሴፍ ያደረጉት ጥናት እንደሚያሳየው፤ በኢትዮጵያ ከአምስት ዓመት በታች ህጻናት መካከል 39 በመቶ የሚሆኑት የመቀንጨር ችግር አለባቸው። ከነዚህም ውስጥ 11 በመቶው በመቀጨጭ የተጠቁ ናቸው ይላሉ።

የመቀንጨር ችግር የሚፈጠረውም ህጻናት ከተወለዱ በኋላ ተመጣጣኝ ምግብ ባለማግኘታቸውና እናት እርጉዝ በነበረችበት ወቅት ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት ባለመከተሏ የሚከሰት መሆኑን ያስረዳሉ። በጥናቱ መሰረት 75 በመቶ የሚሆኑ የሀገሪቱ ህጻናት እስከ ሁለት ዓመት አትክልትና ፍራፍሬ የማያውቁ ሲሆን የተመጣጠነ ምግብ የሚያገኙት ደግሞ ስምንት በመቶዎቹ ብቻ መሆናቸውን እንደሚያትት ያነሳሉ፡፡

ለዚህ ችግር መነሻ ምክንያቱ ማህበረሰቡ ስለ ሥርዓተ ምግብ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን አንስተው፤ ተቋማቸው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚያደርገው ቅኝት ሰዎች በአካባቢያቸው በርካታ ሊበሉ የሚችሉ አትክልትና ፍራፍሬዎች ቢኖሩም እሱን እንደማይመገቡና ከዛ ይልቅም አንድ አይነት የምግብ ይዘት ያላቸው ምግቦችን በተለያየ መልኩ እንደሚመገቡ ነው የጠቆሙት።

በዚህም በበርካታ የሀገሪቱ አካባቢ ያሉ ዜጎች ሊኖራቸው ከሚገባው ክብደት አንሰው ወይም እጅግ በልጠው ፣ ከነበራቸው ተፈጥሯዊ ውበትም ጎድለው እንደሚታዩ ይገልጻሉ፡፡

ይህ ችግር ከገጠራማው አካባቢ ባልተናነሰ በከተማዎችም ላይ የሚስተዋል ሲሆን፤ ለዚህም ምክንያቱ የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦቹን ጠቀሜታ ባለመረዳትና ጣፋጭ ነገር ከመፈለግ የመጣ መሆኑን ያስረዳሉ።

ነገር ግን ሰዎች ምግብን ሲመገቡ ከጣእም ባለፈ ወደ ሰውነታቸው የሚያስገቡት ምግብ ምን አይነት የጤና ጠቀሜታዎችን ያስገኛል የሚለውን ማሰብ እንደሚኖርባቸው ገልጸው፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍም ጤና ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ መከተል እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ፖሊሲው አንድ ሰው በቀን ከ100 እስከ 200 ግራም አትክልትና ፍራፍሬ ፣ 80 ግራም ጥራጥሬ፣ 60 ግራም የእንስሳት ተዋጽኦ መመገብ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

የስነ-ምግብ አማካሪ የሆኑት አብነት ተክሌ እንደሚሉት ደግሞ፤ ምግብ ከመጥገብና ከመራብ ባለፈ በአካላዊና በአእምሮዊ ጤንነት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ለአብነትም በቀን ውስጥ አትክልትና ፍራፍሬዎችን፣ የቅባት እህሎች እና ጥራጥሬን አዘውትረው እና በከፍተኛ መጠን የሚመገቡ እንዲሁም ዶሮ፣ እንቁላል፣ የወተት ተዋፅኦንና ቀይ ስጋን ደግሞ አልፎ አልፎ የሚመገቡ ሰዎች በድባቴና በአእምሮ ጭንቀት የመጠቃታቸው መጠን አነስተኛ ነው ይላሉ፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ዝቅተኛ የአሰር መጠን፣ ከፍተኛ የሆነና ጤናማ ያልሆነ የቅባት መጠን ያላቸውን ምግቦች ፣ ስኳር እና ተፈጥሮአዊ ያልሆኑ ማጣፈጫዎችን የሚመገቡ ሰዎች ደግሞ የስሜት መረበሽ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ይጠቁማሉ።

በአብዛኛው ማህበረሰብም ጤናማ ያልሆኑ ምግቦች ጠቃሚ ተደርገው የሚሳሉ መሆናቸውን ገልጸው፤ ነገር ግን የተለያዩ የምግብ አማራጮች በመጠቀም የተመጣጠነ የአመጋገብ ዘይቤን በመከተል አካላዊም ሆነ አእምሯዊ ጤና መጠበቅ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡

ጤናን መጠበቅ የሚቻለው አንድም በቂ አካላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ እንዲሁም ጤናማ አመጋገብን በመከተል መሆኑን አንስተው፤ በርካቶች በአካባቢያቸው ያለውን የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ ከአላስፈላጊ የጤና ጉዳት እራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን መከላከል እንደሚገባቸው ይገልጻሉ።



# "ታሪካዊው የኢትዮጵያና ሩሲያ…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ታሪክ እና የብዙ ዓመታት የወዳጅነት፣ የመከባበር፣ የሕዝባችን ባህላዊ ቅርበት የታየበት እንደሆነ ተናግረዋል።

ባለፉት ዓመታት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እና በኤጀንሲዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት በመመሥረት ተወያይተናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ሩሲያ ለምታደርጋቸው አብዛኛዎቹ ውጥኖች ኢትዮጵያ የምታደርገውን ድጋፍ እናደንቃለን ብለዋል።

ሩሲያ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥታለች። በሁለተኛው የሩሲያ አፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ላይ የተደረሱትን ስምምነቶችንም ተግባራዊ እናደርጋለን ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ እ.ኤ.አ. በ2023 ከኢትዮጵያ ጋር የተደረገው የንግድ ልውውጥ መጠን በ65 በመቶ መጨመሩን አይተናል ነው ያሉት።

ግንኙነታችን በጤና አጠባበቅና በሳይንሳዊ ምርምር ዘርፎች እንዲሰፋ እንፈልጋለን። የሩሲያ ሸማቾች ኤጀንሲም ከኢትዮጵያ አቻዎቹ ጋር በተለያዩ ፕሮጀክቶች ላይ ተባብረው መሥራት እንዲችሉ ይደረጋል። በዚህም የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ሙያዊ ስልጠና እንደሚኖር ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

የሩሲያ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ሊቀመንበር በሚቀጥሉት ወራት አዲስ አበባን ለመጎብኘት ዝግጁ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# አፍሪካ በምግብ እራሷን ለመቻል በምታደርገው ጥረት ውስጥ የወጣቶች ሚና

**ክብረአብ በላቸው**

በዓለም የምግብ ድርጅት (FAO) ትርጓሜ መሠረት የምግብ ዋስትና ተረጋገጠ የሚባለው በአንድ አገር ያሉ ሁሉም ሰዎች ንቁና ጤናማ ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን በቂ፣ ጤናማና የተመጣጠነ ንጥረ ነገር ያለው የምግብ አማራጭ ለማግኘት የሚችሉበት የኢኮኖሚ አቅምና አቅርቦት ሲኖራቸው ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስምንት መቶ ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ በምግብ እጥረት ችግር ወይም የምግብ ዋስትናው ባልተረጋገጠ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ፣ የዓለም የምግብ ድርጅት ሪፖርት ያመላክታል። ወደ ሁለት ቢሊዮን የሚገመት ሕዝብ ደግሞ ጠቃሚ ቫይታሚኖችንና ማዕድናትን እንደማያገኝ ይገለጻል። ይህ ሁኔታ የተደበቀ ረሃብ (የምግብ እጥረት) (Hidden Hunger) መከሰቻ ተብሎ ይታወቃል።

በአፍሪካ ደረጃ የምግብ እጥረት የሚፈትነው ሕዝብ ቁጥር በጠቅላላው 21 በመቶ ሲሆን፣ ከሰሃራ አፍሪካ በታች ከሚገኙት ውስጥ ደግሞ ከሕዝቡ 25 በመቶ የሚሆነው በምግብ እጥረት ችግር ዕጦት የሚንገላታ መሆኑን አኃዛዊ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከዚህ በተጨማሪም 13 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑ ጨቅላ ሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ በማጣታቸው ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ሲሆን፣ 30 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑ ከዜሮ እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት ደግሞ የቀነጨሩ መሆናቸው የዓለም አቀፍ የተመጣጠነ ምግብ ሪፖርት ያሳያል።

አፍሪካ ዘጠኝ ቢሊዮን ሕዝብ መመገብ የሚያስችል ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬት ባለቤት እንደሆነች ቢነገርላትም፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ አገሮች ይህንን ሀብት በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ሕዝቦቻቸውን ከምግብ እጥረት፣ ከተረጂነትና ከድህነት ማላቀቅና የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል።

የፓን አፍሪካ ባንክ (The Pan-African Bank) ያወጣው መረጃ እንደሚያሳየው፤ አኅጉሪቱ ለእርሻ ተስማሚ የሆነውን 65 በመቶ የሚደርሰውን የተፈጥሮ ሀብቷን በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል ብትችል እ.ኤ.አ. በ2050 ዘጠኝ ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ የሚገመተውን የዓለም ሕዝብ መቀለብ የሚያስችል ዕምቅ አቅም እንዳላት ያትታል። ሆኖም ግን አብዛኞቹ በአህጉሪቱ የሚገኙ ሀገሮች ዋና መለያቸው ረሃብ፣ የምግብ እጥረት፣ የምግብ ዋስትና ማጣትና የመሳሰሉት ክስተቶች ሆነው ዘመናትን ዘልቋል። ይህም አኅጉሪቱ ጤናው የተጠበቀና አምራች ኅብረተሰብ እንዳይኖራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

አህጉሪቷ የራሷን የግብርና ምርቶች በዓለም ገበያ በመሸጥ እንደሌሎቹ ሁሉ ተጠቃሚ የመሆን ሰፊ ዕድል ቢኖራትም፤ ዛሬም የምግብ ዋስትናዋ በከፊል የተንጠለጠለው በውጭ ዕርዳታና ተሸምቶ በሚገባ የምግብ እህል ላይ ነው። በዚህም ምክንያት አኅጉሪቱ ካላት ውስን ጥሪት ላይ በዓመት ወደ 75 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ በማውጣት ለዚሁ ዓላማ ስታውል እንደቆየች የአፍሪካ ልማት ባንክ (African Development Bank) ሪፖርት ይጠቁማል።

ይህንን የአህጉሪቱን ችግር ማቃለል ዓላማው ያደረገና የአፍሪካ የምግብ ዋስትናን መረጋገጥ ግቡ ያደረገ የሺህ አፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ የሚል ስያሜ የተሰጠው የወጣቶች ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በምግብ ሥርዓትና በብዝኃ ሕይወት (በአግሮኢኮሎጂ) ላይ ያተኮረው ይህ የመጀመሪያው የአፍሪካ ወጣቶች ጉባኤ ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የመጡ ወጣቶችን ያሳተፈ ነበር።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) በጉባዔው መክፈቻ ላይ እንዳሉት፤ አፍሪካ በምግብ እራሷን አለመቻሏ ለበርካታ ችግር አጋልጧታል። ከእነዚህም መካከል ተደራራቢ ግጭቶችና ሠላም ማጣት ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህንና ሌሎች ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታትም በምግብ እራስን መቻል ቅድሚያ ተሰጥቶት መሥራት ያለበት ጉዳይ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት ለግብርናው የሚገባውን ያህል ትኩረት ሳይሰጥ ቆይቷል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ሀገሪቱ በምግብ እራሷን ለመቻል በግብርናው ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። በግብርናው ዘርፍ ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ ሜካናይዜሽንን በማበራከት፣ ኩታ ገጠም እርሻን በማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ የግብዓት አቅርቦትን የማሳደግና በወቅቱ ተደራሽ የማድረግ ተግባር መከናወኑን ጠቅሰዋል።

ለአብነትም የማዳበሪያ አጠቃቀም ከነበረበት 13 ሚሊዮን ኩንታል በ2016 የምርት ዘመን ወደ 20 ሚሊዮን ኩንታል ከፍ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል። ዘንድሮ 24 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት መታቀዱን አመልክተው፤ በኢትዮጵያ ያለው የማዳበሪያ አጠቃቀም በአምስት ዓመት ውስጥ በእጥፍ አድጓል ብለዋል። በተጨማሪም የሜካናይዜሽን ሥራውን አጠናክሮ በመቀጠል ከትራክተር ጀምሮ እስከ ወተት ማለቢያ ያሉ ማሽነሪዎችን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በማድረግ ሀገሪቱ በምግብ እራሷን ለማስቻል ቅድሚያ ተሰጥቶት የሚሠራ መሆኑ ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ጉባኤው በዋናነት የምግብ ሥርዓቱን ለማስተካከል ግብርና ላይ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ላይ መሥራት አለበት በሚሉ ጉዳዮች ላይ ለመምከር የተዘጋጀ መሆኑን ያነሱት ፍጹም (ዶ/ር)፤ የአፍሪካ የምግብ ሥርዓትና ሉዓላዊነት በአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ተፅዕኖ እየደረሰበት በመሆኑ የአሕጉሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ግብርናው ላይ እንዴት መሥራት ይቻላል? የሚለው ላይ መፍትሔ ለማምጣት የሚመክር መሆኑን ገልጸዋል።

ጉባኤው በመዲናዋ አዲስ አበባ መካሄዱ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን ለማረጋገጥ የስንዴ እና የሌማት ትሩፋት ንቅናቄዎችን እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ እየተሠራ ያለው አረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ እንዲሁም በቱሪዝም ዘርፉ ያላትን ልምድ ለማካፈል ይረዳል ብለዋል።

ጉባኤውን ያዘጋጀው አላይንስ ፎር ሶቨርኒቲ ኢን አፍሪካ (AFSA) ዋና አስተባባሪ ሚሊዮን በላይ (ዶ/ር)፤ ጉባዔው ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ከ45 የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ ከ250 በላይ ወጣቶች በአካል እንዲሁም ከሁለት ሺህ በላይ ወጣቶች በኦንላይን መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

ጉባዔው የአፍሪካን ግብርና ሥነ ምሕዳርና ብዝኃ ሕይወት መጠበቅን እንደ ዋና ጉዳይ አድርጎ የሚካሄድ መሆኑን ተናግረው፤ አፍሪካ የምግብ ሉዓላዊነቷን ማረጋገጥ እንድትችል ሁሉም የእሴት ሰንሰለት በራስ አቅም ላይ የተመሰረተ መሆን ይኖርበታል ብለዋል።

በጉባኤው ተሳታፊ ከሆኑ ወጣቶች መካከል ከጋምቢያ የመጣው ፋማራ ኮንቴ አንዱ ነው። በጋምቢያ የሚገኘው የአክሽን ኤድ ኢንተርናሽናል የአካባቢ መብቶች ፕሮግራም አስተባባሪ የሆነው ፋማራ ኮንቴ በመላው አፍሪካ የምግብ አቅርቦትን ለማረጋገጥ ወጣቶች ወሳኝ ሚና መጫወት እንዳለባቸው ይናገራል። በተጨማሪም የአፍሪካን የአመጋገብ ችግሮች ለመቅረፍ ቴክኖሎጂን ማላመድ እና ማስፋፋት አስፈላጊ ስለመሆኑ ይገልጻል።

“አፍሪካ በሀብት የበለፀገች ልትሆን ትችላለች። ነገር ግን ሕዝቦቿ አሁንም በድርቅ፣ በረሃብ፣ በግጭት እና በሌሎችም እየተሰቃዩ ነው። እነዚህን ጉዳዮች ለመቅረፍ ወጣቱ ትውልድ ትልቅ ኃላፊነት ሊወስድና በሁሉም ዘርፍ ትብብርን ማጎልበት አለበት። » የሚለው ፋማራ፤ ኮንቴ ለአፍሪካ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብዙ ወጣቶች በግብርና በተለይም ምርትን በማሳደግ ምርታማነትን በማሻሻል ላይ መሰማራት አለባቸው ይላል።

ከመኸር በኋላ የሚደርሰውን ኪሳራ መቀነስ አስፈላጊ ስለመሆኑ የሚናገረው ፋማራ ኮንቴ፤ በምርት አሰባሰብ ሂደት ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ይባክናል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ በቴክኖሎጂ የታገዘ የምርት አሰባሰብ መከተል እንደሚገባ ያስረዳል። በተጨማሪም የአፍሪካ ወጣቶች የአየር ንብረት ለውጥን በመዋጋት ረገድ ንቁ ርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው የሚለው ኮንቴ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የአፍሪካ ስጋት እየሆነ የመጣውን ድርቅ ለመቋቋም የአካባቢ ስነ-ምህዳርን መጠበቅ ያስፈልጋል፤ ለዚህም አገር በቀል ዘሮችን መንከባከብ እንደሚገባ ይናገራል።

> **አፍሪካ ዘጠኝ ቢሊዮን ሕዝብ መመገብ የሚያስችል ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬት ባለቤት እንደሆነች ቢነገርላትም፤ ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ አገሮች ይህንን ሀብት በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ሕዝቦቻቸውን ከምግብ እጥረት፣ ከተረጂነትና ከድህነት ማላቀቅና የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ መልኩ ማረጋገጥ ትልቅ ፈተና ሆኖባቸዋል**

ወጣቱ የአፍሪካን ዘላቂ የምግብ ዋስትና ፍላጎት ወደፊት ለማራመድ ከመንግስታት ጋር በመተባበር እና ተገቢ መፍትሄዎችን በማፈላለግ አብሮ መሥራት አለበት የሚለው ኮንቴ፤ የምግብ ሉዓላዊነትን በራስ አቅም ማረጋገጥ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል ይላል።

ሌላኛዋ የጉባኤው ተሳተፊ በኡጋንዳ የአሳታፊ ኢኮሎጂካል የመሬት አጠቃቀም አስተዳደር (PELUM) ከፍተኛ የፕሮግራም ኦፊሰር ጁልየት ካቱሲሜ (ዶ/ር) የአፍሪካ ወጣቶች (በአግሮ ኢኮሎጂ) ብዝኃ ሕይወት ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለባቸው ትናገራለች።

ብዝኃ ሕይወት ግብርናን ማዘመን ብቻ ሳይሆን አካባቢን መጠበቅ፣ የተፈጥሮ ሥርዓቶችን መረዳት እና ዘላቂነትን ማረጋገጥ መሆኑን የምትናገረው ካቱሲሜ፤ በአህጉሪቱ የምግብ ድጋፍ ለመስጠት በሚል ሰበብና በሰብአዊ ርዳታ ሽፋን የውጭ ኃይሎች እያደረጉ ያሉትን ተጽእኖና ጣልቃ ገብነት ለአፍሪካ ከጥቅም ይልቅ ጉዳቱ እንደሚበዛ ገልፃ፤ "አፍሪካ የራሷ ሃብት አላት፤ ነገር ግን በአግባቡ እየተጠቀመችበት አይደለም። ይህንን አካሄድ ለማስተካከል የአህጉሪቱ ወጣቶች ትልቅ የቤት ሥራ እንደሚጠብቃቸው ተናግራለች።

የአፍሪካ ወጣቶች በአህጉሪቱ የተመጣጠነ አመጋገብ የባህል ለውጥ እንዲመጣ በትኩረት መሥራት አለባቸው የምትለው ካቱሲሜ፤ ከማሳ እስከ ገበያ ያለውን አጠቃላይ ሂደት የሚሸፍኑ ውጤታማ የግብርና ፖሊሲዎች ኖረው በውጤታማነት መተግበር ይኖርባቸዋል ብላለች። ካቱሲሜ ይህ የአመጋገብ ሚዛንን ለማረጋገጥ ወሳኝ ስለመሆኑ ትናገራለች።

በአፍሪካ በሀብት የበለፀጉ እና በድሃ አካባቢዎች መካከል ያሉ ክፍተቶችን በማስተካከል የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ችግርን በመቅረፍ ረገድ መሥራት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ይጠበቃል የምትለው ካቱሲሜ፤ የጋራ ችግርን ለመፈታት የጋራ ትብብር ወሳኝ ነው ብላለች።

ኒዮን ሽኩዛ ሌላኛው ከናሚቢያ የመጣ የጉባኤው ተሳታፊ ወጣት ነው። እርሱ እንደሚናገረው፤ ወጣቶች ከአፍሪካ የሕዝብ ቁጥር አብዛኛው ድርሻ ይይዛሉ። እነዚህ ወጣቶች በመጀመሪያ እራሳቸውንና አህጉሪቱን ለመጥቀም በትምህርት እራሳቸውን ማብቃት ይኖርባቸዋል ይላል።

በተለይ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ የአህጉሪቱን ችግሮች የመቅረፍ ኃላፊነት የወጣቶችም መሆኑን የሚናገረው ሽኩዛ፤ በዚህ ጊዜ እንስሳትን ተጠቅሞ እያረሱ በምግብ እራስን ስለመቻል ማሰብ አዳጋች ነው። ከዚህ አኳያ ዘመናዊ የእርሻ ማሽነሪዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፤ ይህንን ማሽነሪ ደግሞ ሌሎች አምርተው እንዲሰጡ ከመጠበቅ ይልቅ በራስ አቅም ማምረት የሚቻልበትን አቅም መፍጠር ይገባል ይላል።

አፍሪካውያን ከውሃ የአሳ ሀብታቸውን ከመሬት የተለያዩ ማዕድናትን አውጥተው ለመጠቀም የቴክኖሎጂ እገዛ ከምዕራባውያን የሚጠይቁበት ዘመን መብቃት እንዳለበት የሚናገረው ሽኩዛ፤ ሁሉንም ነገር በራስ አቅም የማድረግ ደረጃ ላይ መድረስ ከልታቻለ የሀገራት ሉዓላዊነት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ይናገራል።

የአፍሪካ መንግሥታት በወጣቶች ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል የሚለው ሽኩዛ፤ የብድርና የመስሪያ ቦታ አቅርቦት በማመቻቸት መሥራት ይጠበቅባቸዋል፤ በተለይ በግብርናው ዘርፍ ከሰፋፊ ኢንቨስትመንት ባሻገር ወጣቶች በአነስተኛ መሬት የሚያከናውኑት የግብርና ሥራ ለመደገፍ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው ይላል።

በአጠቃላይ ወጣቶቹ እንደተናገሩት፤ የአፍሪካ መፃዒ ተስፋ የተሻለ ለማድረግ የአህጉሪቱ ወጣቶች የላቀ ሚና መወጣት አለባቸው። አፍሪካ የበለፀገችና የኢኮኖሚ ነፃነቷን ያረጋገጠች እንድትሆን ከመሥራት ባለፈ ሰላሟ የተረጋገጠ አህጉር እንድትፈጠር መትጋት እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

# ከከበሩ ማዕድናት ልማት የመጠቀሚያው ሌላው መንገድ



**የድርጅቱ መስራቾች ይህን ሥራ ስመጀመር አንዱ ምክንያት የሆናቸው ማዕድናቱን በክልሳቸው በቅርበት ሲያገኙዋቸው የሚችሏቸው መሆናቸው ነው። ማዕድናቱ በጥሬው ስገበያ ከሚቀርቡ ይልቅ እሴት ተጨምሮባቸው ቢቀርቡ የተሻለ ተጠቃሚነት እንደሚፈጥር አስቀድመው መረዳታቸውም ሌላው ምክንያታቸው ሆኗል**

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በከበሩ ማእድናት ሀብቶቿ ትታወቃለች። እነዚህ እንደ ኦፓል ያሉት ሀብቶች እየለሙ ያለው በባህላዊ መንገድ ሲሆን፣ ማእድኑ ለውጭ ገበያ የሚቀርብበት መንገድም ምንም አይነት እሴት ባልተጨመረበት ሁኔታ በጥሬው ሆኖ ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እነዚህን የከበሩ ማዕድናት በጥሬው ከመሸጥ በዘለለ፣ እሴት በመጨመር አስውቦና አስጊጦ ለገበያ ማቅረብ ላይ በስፋት እየተሰራ ይገኛል።

ማዕድናቱ እሴት እየተጨመረባቸው ለአንገት፣ ለጆሮ፣ ለእጅ እና ለመሳሰሉት ጌጣጌጥነት እንዲውሉ እየተደረገ ነው። ይህም ጥረት አገሪቱ ካሏት የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ማድረግ እንደሚያስችል በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች ያስገነዝባሉ።

በተለይ የሰሜኑ የአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በእነዚህ ማዕድናት የታወቁ መሆናቸውንና የተለያዩ አካላትም ማእድን በማውጣት ላይ መሰማራታቸውንም በመጥቀስ፣ በእነዚህ ማእድናት ላይ እሴት በመጨመር ስራ ላይ በደንብ መስራት እንዳለበት ይጠቁማሉ። ለዓለም ገበያ ቀርበው ተወዳዳሪ ሊሆኑ የሚችሉ ምርቶችን ለማምረትም ብዙ መስራትን እንደሚጠይቅም ያመላክታሉ። በዚህ ሥራ ላይ ተሰማርተው ለሚሰሩ አካላት ተገቢው ድጋፍና ክትትል ቢደረግላቸው የተሻሉ ሥራዎች በመስራት ለውጦችን ማምጣት እንደሚቻልም ይመክራሉ።

በሀገሪቱ የከበሩ ማዕድናትን በማስዋብና ማስጌጥ ሥራ ላይ ተሰማርተው የሚሰሩ በርካታ ድርጅቶች እንዳሉ ይታወቃል። ከእነዚህ መካካል አንዱ በጎንደር ከተማ የሚገኘው ፍቅሬ ኡስማንና ጓደኞቻቸው የከበሩ ማዕድናትን ማስዋብና ማስጌጥ ሥራ ድርጅት ነው። አቶ ፍቅሬ ሀብቴ እና ሦስት ጓደኞቹ ተደራጅተው የመሰረቱት ይህ ድርጅት የተቋቋመው ከስድስት ዓመታት በፊት ነው። ከድርጅቱ መስራቾች ሁለቱ የብርና የወርቅ ባለሙያዎች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ደግሞ የላፒደሪ (ማዕድናቱን የሚቆርጡና ዲዛይን የሚደርጉ) ባለሙያዎች ናቸው።

የድርጅቱ ሊቀመንበር አቶ ፍቅሬ ሀብቴ እንዳሉት፤ የድርጅቱ መስራቾች ይህን ሥራ ለመጀመር አንዱ ምክንያት የሆናቸው ማዕድናቱ በክልላቸው በቅርበት ሊያገኙዋቸው የሚችሏቸው መሆናቸው ነው። ማዕድናቱ በጥሬው ለገበያ ከሚቀርቡ ይልቅ እሴት ተጨምሮባቸው ቢቀርቡ የተሻለ ተጠቃሚነት እንደሚፈጥር አስቀድመው መረዳታቸውም ሌላው ምክንያት ሆኗቸዋል።

ድርጅቱ ከክልሉ በሚመረቱ የከበሩ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር የማዕድን ስራውን ለማነቃቃት በማሰብ ወደ ሥራው መግባቱን ሊቀመንበሩ ይናገራሉ። ማዕድናት ወደ ማስዋብና ማስጌጥ ሥራዎች ሲገባም ‹‹ሜዳ ›› የተሰኘው የግብረ ሰናይ ድርጅት ድጋፍ እንዳደረገላቸትም ይገልጻሉ፡፡

‹‹ሜዳ›› በማዕድን ዙሪያ የሚሰራ ድርጅት መሆኑን ጠቅሰው፣ ለድርጅታቸው የተለያዩ ድጋፎች ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሰዋል፤ ድርጅቱ በክልሉ ማዕድን ከሚያወጡ ማህበራት ማዕድናት በመውሰድ እሴት በመጨመር የማስዋብና የማስጌጥ ሥራዎችን በመስራት ወደ ተለያዩ ጌጣጌጥነት እንደሚቀየር ይገልጻሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ ወደ እሴት መጨመር ሥራው ከመግባታቸው በፊት በስራው ላይ ያላቸው ውስን እውቀት ነበር። ‹‹ሜዳ ›› በተሰኘው የግብረ ሰናይ ድርጅት ድጋፍ በጎንደር ቴክኒክና ሙያ ተቋም አማካኝነት በማዕድናት ማስዋብና ማስጌጥ ሥራ (የላፒደሪ) ስልጠና አግኝተዋል። ስልጠናው የማእድናቱን አይነትና ባሕሪያት፣ እሴት ማከል፣ መቁረጥና ማስዋብ እና የገበያ ሁኔታን ያካተተ ነበር። የጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች የቢዝነስ ስልጠና እንዲያገኙም እድሉ ተመቻችቶላቸዋል። ከስልጠናው በኋላ ነው በማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ወደ ማስዋብና ማስጌጥ ሥራ የገቡት።

ማዕድናቱን በመቁረጥ፣ ከብር፣ ወርቅ እና ሌሎች ጌጣጌጦች ጋር በመስራት ጌጣጌጦችን የማምረት ሥራን አሃዱ ብለው እንደ ጀመሩ አቶ ፍቅሬ ያስታውሳሉ። እነዚህን ምርቶቻቸውን ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮች ላይ በማቅረብ ያስተዋውቃሉ። በባህር ዳርና በአዲስ አበባ በተዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይ ብዙ ጊዜ መሳተፍ ችለዋል፤ ይህም የገበያ ትስስር ለመፍጠር አስችሏቸዋል።

ኤግዚቢሽንና በባዛሮችን በአብዛኛው የገበያ ትስስሩን ለመፍጠርና ማዕድናቱን ለማስተዋወቅ እንደሚጠቅሟቸው ጠቅሰው፣ ማዕድናቱን በሀገር ውስጥ ገበያ በማስተዋወቅ ሕብረተሰቡ ስለ ማዕድናቱ ግንዛቤው እንዲሰፋ በማድረግ ምርቱ በሀገር ውስጥም ሰፊ ገበያ እንዲኖረው ማድረግ መቻሉን ይገልጻሉ። አግዚቢሽንና ባዛሮቹ ማዕድናቱን ከማስተዋወቅ በዘለለ ምርቶቻቸው በብዛት የሚሸጡባቸው ቦታዎች እንደሆኑም አስታውቀዋል፡፡

በየኤግዚቢሽኖቹና ባዛሮቹ እንድንሳተፍ የተለያዩ ድጋፎች ሲያደርግልን የቆየው አሁን የቆይታ ጊዜውን ያጠናቀቀው ሜዳ የተሰኘው ድርጅት ነበር የሚሉት አቶ ፍቅሬ፤ ድርጅቱ ለሥራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ድጋፎች እንዳደረገላቸውም አስታውቀዋል። እነዚህ ቁሳቁስ ምርታማነታቸው እንዲጨምር እንደሚያስችላቸው አስታውቀዋል። ማዕድናቱ ላይ እሴት መጨመር የሚያስችላቸው እና መሸጫ ቦታ ተከራይተው እየሰሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በጎንደር ቴክኒክና ሙያ ተቋም ወርክሾፕ ተፈቅዶላቸው እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

አቶ ፍቅሬ እንዳብራሩት፤ የማዕድናቱ አይነት የተለያየ እንደመሆኑ እያንዳንዱ ተጠቃሚ የሚፈልገው ማዕድን አንድ አይነት ላይሆን ስለሚችል፣ ከሁሉም በአገሪቱ ከሚገኙ ከበሩ ማዕድናት ልዩ ልዩ ጌጣጌጦችን መስራት ይቻላል። ድርጅቱ በሁሉም አይነት ማዕድናት ላይ በሚባል ደረጃ እሴት በመጨመር የማስዋብና የማስጌጥ ስራ ይሰራል፤ የኦፓል ማዕድን ከዋጋ አንጻር በጣም ውድ በመሆኑ የድርጅቱ አቅም በፈቀደ መጠን የተወሰኑ የኦፓል ጌጣጌጦችን በመስራት ለገበያ ያቀርባል። በተለይ እንደ ጃስበር፣ ሞሳጌት፣ አሜቲስት፣ ኳርትስ እና የመሳሳሉ ከፊል የከበሩ ማዕድናት ከዋጋ አንጻር የተሻሉ ስለሆኑ፣ እነዚህ ላይ እሴት በማከል በብርና በወርቅ በመሰራት ለገበያ ያቀርባል።

ድርጅቱ በከፊል የከበሩ ማዕድናት ለጆሮ፣ ለአንገት እና እጅ ጌጥነት በሚውሉ መልኩ በመስራት ለሀገር ውስጥ ገበያ ያቀርባል። በሀገር ውስጥ ገበያም ቢሆን ግን አብዛኛዎቹን ማዕድናት የሚገዙት የውጭ ሀገር ዜጎች (ቱሪስቶች) ናቸው። በተለይ ማዕድናቱን የሚገዙ የውጭ ሀገር ዜጎች ማዕድናቱ በሀገር ውስጥ ባማረና ውብ በሆነ መልኩ ተሰርተው ሲመለከቱ በጣም ደስተኛ ሆነው እንደሚገዙ አቶ ፍቅሬ ይገልጻሉ፡፡

ማዕድናቱን በክልሉ ካሉ ወረዳዎች ቆፍረው ከሚያወጡ ማህበራት ጋር የገበያ ትስስር ፈጥረው እንደሚገዙ የሚጠቅሱት አቶ ፍቅሬ፣ ኦፓል ከወሎ ደላንታ አካባቢ ሌሎቹን ደግሞ በአቅራቢያቸው ካሉ ወረዳዎች እንደሚያገኟቸው ይገልጻሉ። በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ግን በበቂ ሁኔታ ከአካባቢው እንደሚገኙም ያስረዳሉ፡፡

ድርጅቱ ከመነሻው ጀምሮ እሴት የተጨመረባቸውን የጌጣጌጥ ምርቶች ገበያውን እያሰፋ ለውጭ ገበያ እስከ ማቅረብ /ኤክስፖርት ማድረግ/ ደረጃ ለመድረስ ማቀዱን አቶ ፍቅሬ አስታውቀዋል። ለውጭ ገበያ የማቅረብ ስራ ደረጃቸውን የጠበቁ ማዕድናትን የማምረት ስራንም ይጠይቃል ሲሉ አመልክተው፣ ይህንንም አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ ኦፓል፣ ኤምራልድ፣ ሳፋየር፣ ሩቢ የተሰኙት የከበሩ ማዕድናት በዋጋ ውድ የሚባሉ በግራም እስከ 150ሺ ብር ይሸጡ መሆናቸውን አስታውቀዋል። ጥራት ያለው ኦፓል በግራም ከሁለት እስከ ሶስት ሺ ብር እንደሚያወጣ ጠቅሰው፣ ድርጅቱ እነዚህን ማዕድናት ገዝቶ፣ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የአቅም ውስንነት እንዳለበትና ግብይቱ በሀገር ውስጥ ላይ መወሰኑን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ወርቅ የተለያዩ ደረጃዎች እንዳሉት ሁሉ የከበሩ ማዕድናትም የተለያየ ደረጃ አላቸው። ብርሃን የሚያስተላልፍና የማይስተላልፍ ወይም ድፍን በሚል ደረጃ ይወጣላቸዋል። ሁሉም ማዕድናት የራሳቸው የሆነ ባህሪም አላቸው። አንዱ ማእድን ከሌላው በባሕሪም፤ በዋጋ ከሌላው ይለያል።

አንዳንድ የውጭ ሀገር ዜጎች እሴት ያልታከለበት የከበረ ማእድን መግዛት እንደሚፈልጉ ተናግረው፣ እሴት ጨምረው ሀገራቸው ማሰራት እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። እነዚህ የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ እሴት ተጨምሮባቸዋል የሚባሉ ጌጣጌጦች ክፍተት እንዳለባቸው እንደሚጠቁሙም አስታውቀዋል። ‹ እነሱ የተሟላ የማምረቻ ቁሳቁስ ወይም ቴክኖሎጂ እንዳላቸው አቶ ፍቅሬ ጠቅሰው፣ ማዕድኑን ወስደው አሳምረው በመሰማራትና በከፍተኛ ዋጋ ሊሸጡ የሚችሉበት አቅም እንዳላቸው ተናግረዋል። ሌሎች የውጭ ዜጎች ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ እሴት የተጨመበረባቸውን የከበሩ ማእድናት ጌጣጌጦች ደስ ብሏቸው እንደሚገዙም ገልጸዋል።

አቶ ፍቅሬ እንዳስታወቁት፤ የከበሩ ማዕድናት በባሕሪያቸው አንጻር እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይታወቃል። ጠቀሜታቸውን የሚያወቁ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ዜጎች እየገዙ ይገለገሉባቸዋል። በተለይ የውጭ ሀገር ዜጎች ስለማዕድናቱ ባሕሪያት በጥልቀት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ይጠቀሙባቸዋል።

የኛ ሀገር ሕዝብ የከበሩ ማዕድናትን ከሚገዛ ወርቅና ብር ቢገዛ እንደሚመርጥ ይታወቃል፤ ይህም የሚሆነው ሲቸግረኝ እሸጠዋለሁ ብሎ ስለሚያስብ ነው›› የሚሉት አቶ ፍቅሬ፣ ኢትዮጵያውያን ልክ እንደ ወርቅና ብር ያላቸውን ጠቀሜታ ተረድተው ቢጠቀሙባቸው ተጠቃሚ ይሆናሉ ሲሉ ጠቁመዋል። የሀገራቸውን ምርቶች በሚሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ የሚያስተዋወቁበት አጋጣሚም እንደሚፈጠር ተናግረዋል።

የማዕድናት ጌጣጌጥን በብዛት የሚፈልጉት ቱሪስቶች መሆናቸውን የገለጹት አቶ ፍቅሬ፣ በከበሩ ማእድናት ላይ እሴት የመጨመር ሥራ በሚያካሂዱት አካባቢ በርካታ ቱሪስቶች የክልሉን ጥንታዊ ከተማ ጎንደርን በተደጋጋሚ እንደሚጎበኙ አስታውቀዋል። ይህ ለድርጅቱ ምርቶች ጥሩ ገበያ ሆኖ መቆየቱን ጠቅሰው፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በክልሉ የታየው አለመረጋጋት ቱሪስቶች ወደ አካባቢው በላይ ባሳደረው አሉታዊ ተጽእኖ ሳቢያ ገበያው መቀዛቀዝ ማሳየቱን አመልክተዋል፡፡

አቶ ፍቅሬ ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው በትዕዛዝ ላይ ተመስርቶ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በተለይ አንዳንድ የውጭ ሀገር ዜጎችና ዲያስፖራዎች በሚልኩት ትዕዛዝ መሰረት የከበሩ ማእድናት ጌጣጌጥን እንደሚያመርት ተናግረዋል። እነዚህ የውጭ ዜጎችና ዲያስፖራዎች በተለይ ከልደት ቀናቸው ጋር አያይዞው ከከበሩ ማእድናት ጌጣጌጦች እንዲሰሩላቸው እንደሚፈልጉ አስታውቀው፣ እኛም በሚፈልጉት የማዕድን አይነት የፈለጉትን አይነት ጌጣጌጥና በፈለጉት ዲዛይን እንሰራለን ብለዋል።

ድርጅቱ ቀደም ሲል ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር ትስስር በመፍጠር ይሰራ እንደነበር አስታውሰው፤ ከሌሎች ድርጅቶች ጋርም እንዲሁ እየተነጋገረ ሲሰራ መቆየቱን ገልጸዋል። በቀጣይ የማዕድን ገበያውን በማስፋፋት በትብብር ከሚሰሩት ድርጅቶች ጋር በኦንላይን ገበያ ተደራሽ ለመሆን እየሰሩ መሆኑንም አስታውቀዋል። በቀጣይ እሴት የተጨመረባቸው የከበሩ ማእድናት ምርትና ምርታማነት በማሳደግ እንዲሁም የገበያ ተደራሽነቱን በማስፋት እነዚህን ጌጣጌጦችና ማዕድናት በቀጥታ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ድርጅቱ አቅዶ እየሰራ መሆኑን አቶ ፍቅሬ ጠቁመዋል።

በአገሪቱ የተለያዩ ዓለም ላይ የማይገኙ እጅግ የከበሩ ማእድናት በስፋት እንደሚገኙ ጠቅሰው፣ ይህን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ አስገንዝበዋል። በተለይ በከበሩ ማእድናት ላይ እሴት በመጨመር ስራ የተሰማሩ አካላትን በመደገፍና ምርቶቹን ለውጭ ገበያ በስፋት በማቅረብ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬን ማግኘት እንደሚቻልም አቶ ፍቅሬ አመልክተዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የኛ ቤት ጀበና

ሀብታሙ ባንታየሁ

እሳት ያተከነውን ጀበና ከምድጃው ላይ መንጥቃ አወጣችው። ቻይነቱ ይገርማል፤ እየተጠበሰም ቢሆን ፍልቅልቅ ፈገግታውን ይጋብዛል። ቡና ቀዳችና ከቆሎውም፣ ከቂጣውም፣ ከልስሱም ቆንጥራ ቆሌ ተቋደስ ብላ በአራቱም ማዕዘን ረጨችው። ይህን ያደረገችው ከቆሌ በፊት ሰው ከቀመሰው አዝመራውን፣ ልጅና ከብቱን ይጣላልና ነው። አቦል ጀባ አለችና የጀበናውን ጆሮ ስማ ወስከንባዩን ብትከፍተው ሞሰብ ወርቁ በህብስት ተጨንቋል። "የቆራሽ ያለህ ..." አለች እንዴ ደጁን አንዴ ህብስቱን አትኩራ እያየች።

በባህሉ በቤቱ አባወራ ከሌለ ሌላ ወንድ ቡና ጠጭ መጠበቅ ግድ ነው። በስመ ስላሴ ባርኮ ከሰጣት በኋላ እንጂ ሴት ልጅ ከወንድ ቀድማ እጇን ወደ ሞሰቡ አትሰድም፤ እማማ ጦቢያውንም የጠበባት ይህ ነው። እንኳን በበዓል ወቅት ባዘቦትም ሰው የማይለየው አዳራሽ ወና ሆኗል። ተራውጠው ያደጉበት ልጆች ዛሬ የሉም፤ መብሉ መጠጡ ሞልቶ ተርፎ ሳለ አይናን ሰው እራበው። ደጅ ደጁን ብታይ ዝር የሚል ጠፋ፤ ተንገበገበች። "ለካ... ጊዜ ሲጥል እንዲህ ነው፣ ተናፋቂ እንዳልነበርኩ ናፋቂ ልሁን?" አለች ከንፈሯን ነክሳ። "ልጆቼን የሰው ሰራሽ ወረቀት ቢያስኮበልላቸው የወላድ መካን ተባልኩ" ውጋት እንደያዘው ወዲያ ወዲህ እየተንቆራጠጠች "ምነው ጌታዬ... ብትወደኝ ነው ብትጠላኝ ፈተናዬ መብዛቱ? ባውዳመቱ ምድር ባይተዋርነት ቤቴን ሲወረው እንዴት ፈቀድክ?" ከደም የወፈረ እንባ ጉንጯን አራሰው። በሐዘን ብዛት ደንዝዛለች፤ ከቀልቧ አልነበረችም። ተንጋግተን ከቤቷ ስንገባ እንኳን አልሰማችም። ሴት ልጇ ከወደ ኋላ ቆማ እጇን በፊት ለፊት ሰዳ አይናን በመጨፈን "እንኳን አደረሰሽ እናቴ" ስትላት ከሰመመን ነቃች።

ያብራኳ ክፋዮች እጅ እየነሳናት ስታይ ዳግም የደስታ እንባ አነባች። ለቅሶ ቤት ነው እንዴ የመጣነው? ብዬ ገሰፅኳት። እንባዋን አደራርቃ የበረደውን ቡና ጣደችና የዶሮ አይን የመሰለ ጠላ አሲይዛን ከበናት ተቀመጥን። ቤት ያፈራውን ስታቋድሰን እኛ ደግሞ ስጦታ አበረከትንላት። የመጀመሪያውን ሀጎስ "እናቴ ላውዳመቱ እንኳን አደረሰሽ" ብሎ የያዘውን ሻማ ዘረጋላት።

አንዴ ሻማውን አንዴ እሱን እያች "ሻማ በቀን ምድር ምን ይሰራል?" አለችው። "በቃረምኩት እውቀት የጋረደንን ያስተሳሰብ ጨለማ እንደሻማ ቀልጬ እገፈዋለሁ" ብሎ ቃል በመግባት ጫንቃ ሳመ። አጫሎ ደግሞ ከደጅ ያኖረውን በትር አምጥቶ አስረከባት። "አቅሜ ሳይዝል መቋሚያ ለምኔ?" ብትለው ታናሾቹ የሚደገፉት፣ ታላቆቹ የሚመረኮዙት ጠንካራ ትውልድ እንደሚሆን ቃሉን ሰጣት። እኔም የበኩሌን ሰነዘርኩ። የታሸገውን ካርቶን ብትፈታው መአት ኮንዶም ነው፤ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ... ለኔ ኮንዶቭ?" አለችና አሽቀነጠረችው። እታተይ ብዬ ጠራኋትና እራሴን ከበሽታ በመጠበቅ ጤናማ ትውልድ ለመፍጠር እጥራለሁ በማለት ኪዳን አሰርኩ። ቀጥላ እህታችን ጅንስ ሱሪ አሳቀፈቻት። ምን አልኩሽ ልጄ? በሚል አስተያየት ተመለከተቻት። "ጥበብ ቀሚሱን አሸሞንሙኖ ያለበሰኝ እጅሽ እንዳይገፋኝ ከእንግዲህ ወዲያ ሱሪ አልደነቅርም ብላ ጉልበት ሳመች። በመጨረሻም ሁሴን ባንዲራና ጩቤ ይዞ ከፊቷ ቆመ። "ደግሞ ምንድን ነው እሱ?" አለች አይናን ተከላበት። " የክብር ልብስሽን ለማውለቅ ከሚያሴሩት ጋር አብሬ የበላሁ እንደሆነ ያባቴ ቃል እርግማን ይሁንብኝ፣ አጥንቱ እሾህ ሁኖ ይውጋኝ" አለና ፉከራ ቢጤ አስከተለ።

"እውነት ከእውነትነቱ ለማይሻገር፣
ለሰው ሰራሽ ወረቀት ከምግደረደር፣
የድሃ ልጅነቴን ይዤ ልቀበር። "

ወደኛ እየጠቆማት የቱንም ያህል ከባድ ችግር ቢሆን በውይይት ከመፍታት በቀር ከወንድሞቼ ጋር ደም ላልቃባ ቃል እገባልሻለሁ ብሎ የያዘውን ጩቤ ሰባብሮ እግሩ ስር ጣለና የክብር ልብስ አጎናጸፋት

እየተፍለቀለቀች "ልጆቼ ማለፊያ እውቀት ገብይታችሁ መጥታችሁልኛላ!" አለችን።

የበዓሉን ሽርጉድ እንዳዲስ ጀመረችው። ቆራሽ ያንቃቃ የነበረውን ህብስት ከፊታችን ሰየመችው። ሁላችንም ተፈራራን። ከተለያየ አባት መወለዳችንን እንጂ አንድም ቀን የአንድ እናት ልጆች መሆናችንን አስበን ተፈቃቅደን አናውቅም። አማትቤ ድፎውን ልቆርጥ ቢላ ሳነሳ ሀጎስ እጄን ያዘኝ።

ኧረ ተይ እገሊት ጡር ፍሪ ጡር ፍሪ፣
ታላቅ ተቀምጦ ታናሽ አትዳሪ።

ተብሎ መዘፈኑን አጣኸው?" አለ ሞሰቡን ወደ ራሱ እየሳበ። ታላቁ ያላገባ እንደሆነ ታናሹ ቁሞ መቅረት አለበት? ብዬ አሾፍኩበትና ተራዬን እጁን ይዤ "አንተስ ማን ስለሆንክ ትቆርሳለህ? ብዬ ከለከልሁት።

በመልካም ስራ ለተምሳሌትነት የበቃ ዕድሜ ሲያስከብር የእንጨት ሽበት የወረሰው ዕድሜ ባንጻሩ ያስንቃል። ወጣቱ ኃይል የሚሰደደው በሀገሩ መኖር ጠልቶ መሰለህ? ቀድሞ በመወለድ የሚያምነው የዕድሜ ክልል ጥቅሙን ላለማጣት ሲል ልጅ ያቦካው ለራት አይበቃም፣ ልጅ ቢሮጥ አባቱን አይቀድምም እያለ ያሸሸዋል እንጂ አያቀርበውም፣ እና... ብሶቴን በዳቦው ብገልጽ ምን ይመስልሀል? አልኩትና ሞሰቡን ወደኔ አንኳተትኩት። ሽንፈት መስሎት እልህ ተጋባ፤ መልሶ አንሻቶ ወሰደው። ሁሴንም ጣልቃ እየገባ "እናንተ ከምትጣሉ ከሁላችሁም እኔ ቀይ ስለሆንኩ ልቁረሰው" ብሎ እጁን ሲያሾል ማንነት ባስተሳሰብ እንጂ በቀለም አይለካም ብዬ ዝም አሰኘሁት። አጫሎ እኔም ይድረሰኝ ይመስላል፤ "ከሁላችሁም ወፍራሙ እኔ ስለሆንኩ ብቆርሰውስ?" አለ በተራው። የአፈር ክምር ገለባው እንጂ ፍሬው መቼ ታይቶ ያውቃል? በማለት በነገር ጎሸምኩት።

ኡፋይሴም "ቅድሚያ ለሴት" ብላ ልትቆርስ ቢላውን ጨበጠች። እጇን አረገፍኳትና የምናከብረው ማርች ኤይት አይደለም አልኳት። "ማለት?" ብላ ነገር ልታከር ስትል ማለት ተብሎ አረፍተ ነገር አይጀመርም ብዬ ደሰኮርኩና ዝም እንድትል ባይኔ ዛትኩባት። እናታችንም ሁኔታችን አልጥምሽ ቢላት በትዝብት ታየናለች። ከፊቷ ጥሩ ስሜት አይነበብም፤ ግንባሯ ተኮሰታትሯል። ዳቦውን ለመቁረስ ሁሉም የሰጡት ምክንያት አሳማኝ ባለመሆኑ እራሴው ልቆርሰው ካራውን ሳሰናዳ እነሱም ግንባር ፈጥረው አበሩብኝ። እቆርሳለሁ አትቆርስም ስንኳተት ሞሰቡ ተከነበለ። በድርጊታችን የእናታችን ሐዘን አገረሸ። እናታችን "በጠባችሁት ጡቴ ይዣችኋለሁ፤ ...

የእሳቱ ፍም ጀግንነታችሁ፣
የጀበናው ገላ ጥቁር እንቁነታችሁ፣
የፍንጃሉ መልክ ዘላቂ ሰላማችሁ፣
ይሁነኝና ለሀሳቤ አንድምታ፣
ማህጸኔ እንዳይረገም የማታ ማታ፣
እንድኖር ብትሹ እድሜ ልኬን ተደስቼ፣
በአድባሩ ፊት ይቅር ተባባሉ ልጆቼ።
አለችን ተስፋ ሰንቃ፣
እያየችን አፈራርቃ።

እኛ ግን የጋለበን ሰይጣን ከላያችን አልወርድ ብሎ መናቆሩን ቀጠልን።

ስንብላላ የሰሙ አንድ አዛውንት "ቤቶች እንኳን አደረሳችሁ" ብለው ገቡ። ጩኸታችን መበርከቱን ገልጸው ምን እንደሆን እናታችንን ጠየቋት። እሷም የለቅሶዋን ሰበብ አንድም ሳታስቀር አዋየቻቸው። አዛውንቱም "ልጆቼ...ቀርቦ ከመገፋት ተወዶ ከመጠላት ይሰውራችሁ፣ታምኖ ከመጠርጠር አግኝቶ ከመቸገር ይጠብቃችሁ፣ የራስን ከመዘንጋት የሰውን ከመመኘት ያውጣችሁ፣ ብዙ ከማውራት ብዙ መስራት ያልምዳችሁ፣ አዋቂ እንጂ ታዋቂ ለመሆን አትጣሩ፣ ስራችሁ አፍ አውጥቶ ይናገራልና " እያሉ ምርቃትና ምክር ቀላቅለው ሲገስጹን ቆይተው ጦቢያ ትቅደም ብለን ህብስቱን በጋራ እንድንቆርሰው አዘዙን፤ እንዳሉን አደረግን። የእናታችን ፈገግታ እንደ ጸሀይ ብርሀን ሞቀን። እንትፍ እንትፍ ተብሎብን ቆሌ እርቀ ሰላም ሲያወርድ አዛውንቱንና እናታችንን ከመሀል አድርገን በእጃችን እንግጫ ይዘን...

አንቺ ኢትዮጵያ... ውዲቷ ቆንጆ ሀገራችን፣
በሦስቱ ቀለም ሰንደቅ አላማችን፣
እንዘምርልሻለን በሙሉ ልባችን፣
ሀሳብሽን እንፈጽመው በትግላችን።
ኢትዮጵያ እናታችን ደግ ወላድ እናት፣
ወልዳ የምታሳድግ በማር በወተት፣
ልጆቿ ፋፍተዋል በእርሷ አሳቢነት፣
ይኸው ተሰብስበው ያሳያሉ ህብረት።
ህብረታቸው ፅኑ ሰውን የሚያስቀና፣
ኢትዮጵያም ደስ አላት በእነርሱ ትህትና።
ኢትዮጵያ እምነቷን ስትጥል በእኛ ላይ፣
መበርታት አለብን እንዳንሆን አባይ።

አፍ የፈታንበትን ዜማ ዳግም አንቀረቀርነው። ድንገት እትዬ ባንቺ አይሞሉ በሬን ሲያንኳኩ ከእንቅልፌ ነቃሁ። የቅዥቴን ምንጭ ሳስስ ከራስጌ አገኘሁት፤ ለካስ አያቴ ስትነግረኝ አልሰማ ብዬ ሱሪዬን ተንተርሸው ኖሯል። በህልሜ የዘመርኩላትን ውብ ኢትዮጵያዬን ብፈልጋት ከልቦለድና ከዘፈን ውጪ አጣኋት።

# ዓለም አቀፍ

## ፑቲን ሩሲያን ለመነጠል የምዕራባውያኑ ጫና እየሠራ እንዳልሆነ እያሳዩ ነው

ምዕራባውያን በሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ምክንያት ሩሲያ ከዓለም የኢኮኖሚ ሰንሰለት እንድትነጠል ለማድረግ ሌት ተቀን እየሠሩ ይገኛል። ማዕቀቦችን በመጣል የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብትን ከዓለም አቀፉ ገበያ ጋር ያለውን ትስስር እንዲቋረጥ ለማድረግ ሞክረዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት በጦር ወንጀል ክሶች የእስር ማዘዣ በሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ላይ አውጥቶባቸዋል። የምዕራቡ ዓለም ጫና እና ግፊት እየሠራ ይሆን? ጊዜ የሚፈታው ይሆናል። ጫናውን መቋቋም እንደሚችሉ የሚናገሩት ፑቲን ከሰሞኑ የብሪክስ ጉባኤን በሀገራቸው አስተናግደዋል። ከጥቅምት 12 -14 ቀን 2017 ዓ.ም በተካሄደው የብሪክስ ጉባኤ አባል ሀገራቱ በሩሲያዋ ካዛን ከተማ ተሰብስበዋል።

የቻይናው መሪ ዢ ጂንፒንግ፣ የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ እና የኢራን ፕሬዚዳንት ማስዑድ ፔዜሽኪያን እና በፈጣን ዕድገት የሚገኙ ከ20 በላይ ሀገራት መሪዎች በዚህ ጉባኤ ላይ ይታደማሉ። ክሬምሊን በሩሲያ ከተደረጉ "ታላላቅ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ክስተቶች አንዱ" ሲል ነው ጉባኤውን የጠራው። በዚህ ጉባኤ "ማስተላለፍ የተፈለገው ግልጹ መልዕክት ሩሲያን ለማግለል የተደረገው ሙከራ አልተሳካም የሚል ነው" ይላሉ በጂኦ ፖለቲካ እና ፖሊሲ ላይ የሚያተኩረው ማክሮ አድቫይዘሪ የተሰኘው ድርጅት መሥራች ክሪስ ዌፈር።

"ሩሲያ ማዕቀቦችን ተቋቁማ አይበገሬነትዋን እያሳየች እንደሆነ ከክሬምሊን የተላከ ትልቅ መልዕክት ነው። ከውጭ እንደሚታየው ሳይሆን በሀገሪቷ ውስጥ ከባድ ስንጥቆች እንዳሉ እናውቃለን። ነገር ግን በጂኦፖለቲካዊ ዕይታ ሩሲያ ወዳጆች እንዳሏት ማሳያ ነው። እነዚህም የሩሲያ አጋሮች ይሆናሉ" ይላሉ።



ብሪክስ የሚለው የእንግሊዝኛ ምኅጻረ ቃል አባል ሀገራቱን ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ እና ደቡብ አፍሪካን የሚያመለክት ነው። የምዕራቡን ዓለም መሪነትን በመጻረር እንዲሁም ፍትሐዊ ዓለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍ እንዲኖር በማለት የተመሠረተ እንደሆነ የሚነገርለት ብሪክስ፤ አድማሱን በማስፋት ግብፅን፣ ኢትዮጵያን፣ ኢራንን እና የተባበሩት አረብ ኤምሬትስን በአዳዲስ አባልነት ተቀብሏል። ሳውዲ አረቢያም የሀገራቱን ጥምረት እንድትቀላቀል ተጋብዛለች።

የብሪክስ አባል ሀገራት የዓለማችን 45 በመቶ ሕዝብ ይኖርባቸዋል። የሀገራቱ ምጣኔ ሀብት ሲደመርም ከ28.5 ትሪሊዮን ዶላር በላይ ሲሆን፣ ይህም የዓለማችንን 28 በመቶ ምጣኔ ሀብት አካባቢ ነው። የሩሲያ ባለሥልጣናት ሌሎች ተጨማሪ 30 ሀገራት ብሪክስን ለመቀላቀል ወይም ከድርጅቱ ጋር ጠንካራ ግንኙነት መመሥረት እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። አንዳንዶቹም እነዚህ ሀገራት በጉባዔው ላይ ተሳታፊ ናቸው።

በሩሲያ ካዛን በተካሄደው ጉባኤ ከተንጸባረቁ ጉዳዮች አንዱ ብሪክስ ምን ያህል "አብዛኛውን የዓለም ሕዝብ" እንደሚያቅፍ ይጠቀሳል። ጉባኤው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በጂኦ ፖለቲካዊ መድረክ ያላቸውን ስፍራ ከማሳየት ውጪ ምን ፋይዳ ሊኖረው ይችላል? የምዕራባውያንን ጫና ለመቀልበስ የሚፈልጉት ፑቲን ለዓለም አቀፍ መገበያያዎች ከዶላር ሌላ አማራጭ ገንዘብ እንዲኖር የብሪክስ አባል ሀገራትን ለማሳመን ተስፋ ማድረጋቸው ተገልጿል።

ሆኖም ተቺዎች በብሪክስ አባል ሀገራት ውስጥ ያለውን ልዩነት በመንቀስ "ፍጹም ተመሳሳይ አቋም" የያዙ አይደሉም ይላሉ።"በአንዳንድ መንገዶች ቻይና እና ሕንድ በማንኛውም ነገር መስማማት አለመቻላቸው ለምዕራቡ ዓለም ጥሩ ነው። ምክንያቱም ሁለቱ ሀገራት ቢስማሙ ብሪክስ በዓለማችን ላይ ታላቅ ተጽእኖ ማሳደር ይችል ነበር" ሲሉ የአሜሪካው ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ባንክ እና የፋይናንስ አገልግሎት የሆነው ጎልድማን ሳክስ የቀድሞ ዋና የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ጂም ኦኔል ይገልጻሉ።

"ቻይና እና ሕንድ አብዛኛውን ጊዜ እርስ በርስ ለመጠላለፍ የሚያደርጉትን ጥረት ለመቀነስ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ። እነዚህን ሀገራት በምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮች ላይ ትብብር እንዲፈጥሩ ማድረግ የከበደ ፈተና ነው" ሲሉ ጂም ኦኔል ያስረዳሉ። ጂም ኦኔል ብሪክ የሚለውን ምኅጻረ ቃለ ለአራት በፈጣን ዕድገት ላይ ላሉ ሀገራት ሲያልሙት የነበሩ ሲሆን፣ ሀገራቱ ወደ ዓለም አቀፉ የፖሊሲ ውሳኔ እንደሚመጡም ያምኑ ነበር።

"የሩሲያ የምጣኔ ሀብት እያጋጠመው ያሉ ችግሮች የወጭ ንግድ እና ክፍያ ጋር የተገናኙ ናቸው። አብዛኛው ደግሞ ከአሜሪካ ዶላር ጋር ቁርኝት አለው" ይላሉ ዌፈር። "የአሜሪካው ግምጃ ቤት በዓለም ንግድ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው፤ ምክንያቱም ዋነኛ መገበያያ ገንዘቡ የአሜሪካ ዶላር ስለሆነ ነው። የሩሲያ ዋነኛ ፍላጎት የአሜሪካን የዶላር የበላይነት መስበር ነው።

"ለዚህም የብሪክስ ሀገራት አማራጭ የንግድ ዘዴ እንዲዘረጉ እና ዶላር፣ ዩሮን ወይም የትኛውንም የቡድን 7 ሀገራት ገንዘቦችን ያላከተተ የወጭ ንግድ እና የመገበያያ ሥርዓት እንዲኖር ትፈልጋለች። በዚያውም ማዕቀቡንም ጥርስ አልባ ማድረግ ነው" ሲሉ ማስረዳታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# በበጎ እሳቤ ድንበር የለሽ በጎ ተግባርን የማዳረስ ጥረት

**አንተነህ ቸሬ**

ድህነትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለተንሰራፉባቸው ማኅበረሰቦች፣ የበጎ አድራጎት ተግባራት የማኅበራዊ ፈውስ ሁነኛ መገለጫዎችና መሳሪያዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የበጎ አድራጎት ተግባራት ገንዘብን፣ ፍቅርን፣ ጊዜንና ሌሎች ሀብቶችን ከራስ ቀንሶ ለሌሎች በማካፈል የሌሎችን ችግር ለማቃለል፤ ፍቅርን፣ መተሳሰብንና አንድነትን ለማጠንከር እንዲሁም መተሳሰብና መከባበር የሰፈነበትን ማኅበረሰብ ለመፍጠር የማይተካ አወንታዊ ሚና አላቸው፡፡

መረዳዳት የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆነና የእርስ በእርስ ማኅበራዊ መስተጋብራቸውን አጠንክሮ የኖረ ተግባር ነው፡፡ መረዳዳት ባይኖር ኖሮ አሁናዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አሁን ከሚታየው የተለየ ይሆን ነበር፡፡ ይህ መረዳዳትና መተጋገዝ በብዙ መንገዶች ይከወናል፡፡ በተናጠልና በጥቂት ግለሰቦች ስብስብ ከሚከናወኑ የመረዳዳት ተግባራት በተጨማሪ፣ መደበኛና ሕጋዊ አሰራሮችን ተከትሎ የበጎ አድራጎት ተቋማትን የማቋቋምና የመስራት ተግባርም በስፋት የሚታወቅ አሰራር ነው፡፡

ችግሮችን ተቋቁሞ ለማለፍ ብርታት የሚያጥራቸው ሕፃናትና አረጋውያን፣ ለብዙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፡፡ አካላቸውና አዕምሯቸው ያልጠናው ለጋ ሕፃናት እና ብዙ ደክመው በማምሻ እድሜያቸው ላይ አቅም የከዳቸው አረጋውያን፣ የቤተሰብና የዘመድ እንክብካቤ በሚፈልጉበት የእድሜያቸው ምዕራፍ ላይ ለችግር ተጋላጭ ሲሆኑ ችግሮችን የሚቋቋሙበት ብርታት አያገኙም፡፡ የበጎ አድራጎት ተግባራት እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለማቃለል በዋጋ የማይተመን ሚና አላቸው፡፡ «ድንበር የለሽ የበጎ አድራጎት ማኅበር» የተሰኘው ምግባረ ሰናይ ድርጅት የተመሰረተው የሀገር ተረካቢና የሀገር ባለውለታ የሆኑትን እነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች በዘላቂነት ለማገዝ ነው፡፡

የማኅበሩ የቁጥጥር ኦዲተር አቶ ምህረት ታከለ «ድንበር የለሽ» የበጎ አድራጎት ማኅበር በዋናነት አረጋውያንን፣ ወጣቶችንና ሕፃናትን በመርዳት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እንደሚገኝ ይገልፃሉ፡፡ ድርጅቱ የተመሰረተው «በጎ እናስብ/Think Positive» በሚል መሪ ቃል በ15 በጎ ፈቃደኛ አባላት፣ በኅዳር 2006 ዓ.ም ነው፡፡

የማኅበሩ ዓላማዎች በጎ ፈቃደኝነትን ማስፋፋት፣ ሱሰኝነትን መከላከል፣ ንቁ ዜጎችን ማፍራት፣ ባህልና ወግን ማስጠበቅ፣ ጾታዊ ጥቃትን መከላከል፣ መተሳሰብ፣ መከባበርና መረዳዳትን ማጎልበት እንዲሁም ሰላም ወዳድ ማህበረሰብን ማፍራት ናቸው፡፡ የማኅበሩ ዋና ቢሮ ባህር ዳር ከተማ የሚገኝ ሲሆን፣ በአማራ ክልል በ10 ከተሞች ቅርንጫፎችን ከፍቶ ዘርፈ ብዙ የበጎ አድራጎት ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከአምስት ሺ በላይ አባላትም (የማህበሩ መታወቂያ ያላቸው) አሉት፡ ፡

«ሁሉም ሰው በጎ ፈቃደኛ እንዲሆን እናስተምራለን፡፡ ኪነጥበብን በመጠቀም ሰዎች ከሱሰኝነት የሚላቀቁበትን መፍትሄ ለማበጀትም እንሰራለን፡፡ ወጣቶች ሳምንቱን ሙሉ መጻሕፍትን እየተዋሱ እንዲያነቡ በማድረግ የአስተሳሰብ አድማሳቸው እንዲሰፋ ለማደረግ እንጥራለን» ሲሉ ምኅረት ይናገራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ማኅበሩ ፍላጎት ኖሯቸው ገንዘብ ከፍለው መሰልጠን ለማይችሉ ወጣቶችና ታዳጊዎች ኢትዮጵያዊ ግብረ ገብነትና የትወና ስልጠናዎችን ለ12 ዙሮች በነፃ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ታዳጊዎችና ወጣቶች አለባበሳቸው ጭምር ምክንያታዊና ባህልና ወግን የጠበቀ እንዲሆን ያስተምራል፡፡

ሁሉንም ነገር ማድረግ የሚቻለው ሰላም ሲኖር ብቻ በመሆኑ ስለሰላም አስፈላጊነት ይሰብካል፡፡ የበጎ ስራ ተግባራት ከዕለታዊ ድጋፍ ተሻግረው በግለሰቦች ሕይወትና በማኅበረሰብ ኑሮ ላይ ዘላቂ ለውጥ እንዲያስገኙ ኅብረተሰቡ፣ የበጎ አድራት ተቋማት፣ ድጋፍ ፈላጊዎችና መንግሥት የየራሳቸው ኃላፊነቶች እንዳሉባቸው ያስገነዝባል፡፡

ማኅበሩ በዋናነት ትኩረት የሚያደርግባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ህፃናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን እንደሆኑ የሚናገሩት አቶ ምኅረት፣ 100 አረጋውያንን ያለማቋረጥ እየደገፈ እንደሆነና 104 ተማሪዎች በየቤታቸው ሆነው ትምህርት እንዲማሩ እያደረገ እንደሚገኝ ይገልፃሉ፡፡ ወጣቶች ከሱስ ተላቅቀው የልብስ ስፌት፣ የውበት እና የመኪና አሽከርካሪነት ስልጠና በነፃ እንዲያገኙም አድርጓል ሲሉ ጠቅሰው፣ ወጣቶቹ ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ በመንግሥት ተቋማትና በግል ድርጅቶች ስራ አግኝተው እየሰሩ እንደሚገኙም ነው ያስታወቁት፤ ከሱስ ተላቅቀው ስራ ይዘው ማኅበሩን ማገልገላቸው ትልቅ ስኬት እንደሆነም አቶ ምኅረት ይናገራሉ፡፡




አቶ ምኅረት እንዳስታወቁት፤ ማህበሩ በዋናነት በባህር ዳር ከተማ የበጎ ፈቃደኝነት አስተሳሰብ በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲሰርፅ በማድረግ በብዙ ሺዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች የአልባሳት ድጋፍ አድርጓል፡ ፡ ለአብነት ያህል ንብረታቸው ለተቃጠለባቸው የአጣየ ከተማ ነዋሪዎች 47 ኩንታል ልብስ እንዲሁም ቻግኒ ከተማ ለነበሩ ተፈናቃዮችም አልባሳት ሰጥቷል፡፡ ለራያ ቆቦ ነዋሪዎችም ልዩ ልዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ በጦርነት ለተፈናቀሉ ወገኖች የአልባሳትና የሌሎች ቁሳቁስ ድጋፎች ተሰጥተዋል፡፡

«በዋናነት የምንሰራው ድጋፍ ላይ ነው፡፡ ወደ ማኅበሩ ቢሮ መምጣት ላልቻሉ ሰዎች የቤት ለቤት ድጋፎችን እናደርጋለን» ሲሉም ጠቅሰው፣ «ከጥገኝነት ነፃ የሆነ ትውልድ ይፈጠር ዘንድ በሰው አዕምሮ ላይም እንሰራለን፤ በጎ ካሰብንና በጎ ነገሮችን ማድረግ ከቻልን፣ ሰው ከጥገኝነት መላቀቅ እንደሚችል በማመን እንሰራለን» ይላሉ፡፡

«ድንበር የለሽ» የበጎ አድራጎት ማኅበር ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ባከናወናቸው ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ባሏቸው ማህበረሰብ ተኮር ተግባራት የበርካታ ሰዎች ሕይወት በበጎ ተለውጧል፡፡ አቶ ምኅረት እንደሚገልጹት፣ ማኅበሩ ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከ200ሺ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ ይህ አሀዝ ግን ዘላቂ ጥቅም ያስገኙትን ድጋፎች ብቻ እንጂ ጊዜያዊ ድጋፎችን (ለአብነት ያህል በበዓላት ወቅት የሚደረጉ ጊዜያዊ ድጋፎች) የሚያካትት አይደለም፡፡

ማኅበሩ ለበጎ አድራጎት ስራዎቹ መከወኛ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በሦስት መንገዶች እንደሚያገኝ አቶ ምኅረት ያስረዳሉ፡፡ የአባላት መዋጮ አንዱ የገንዘብ ማግኛ መንገድ መሆኑን ጠቅሰው፣ የማኅበሩ አባላት በየወሩ ከ15 ብር ጀምሮ እስከ አንድ ሺ ብር (የወርቅ ደረጃ አባላት) እንደሚያዋጡም ገልጸዋል፡፡ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚኖሩ ወገኖች ድጋፍ ማግኘት ነው ያሉት አቶ ምኅረት፣ ለተቋማት ደብዳቤ በመፃፍ ድጋፍ የመጠየቅ አሰራርም ማኅበሩ ለበጎ አድራጎት ስራዎቹ የሚያስፈልገውን ገንዘብ የሚያገኝበት ሌላው መንገድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**ማኅበሩ ስራውን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከ200ሺ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል፡፡ ይህ አሀዝ ግን ዘላቂ ጥቅም ያስገኙትን ድጋፎች ብቻ እንጂ ጊዜያዊ ድጋፎችን (ለአብነት ያህል በበዓላት ወቅት የሚደረጉ ጊዜያዊ ድጋፎች) የሚያካትት አይደለም**

«ማኅበሩ መንግሥት መሸፈን ያልቻላቸውን ችግሮችና ክፍተቶችን የሚሞላ በመሆኑ፣ መንግሥት ብዙ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል» የሚሉት አቶ ምኅረት፣ «መንግሥት ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የስልጠና እድሎችን ያመቻቻል፡፡ ማኅበሩ ለሚያቀርባቸው የቦታና ሌሎች ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡፡ የማኅበሩ አባላት ደህንታቸው ተጠብቆ የበጎ አድራጎት ስራዎችን እንዲያከናውኑ የትብብር ድብዳቤዎችን በመፃፍ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ጣና ክፍለ ከተማ፣ ሽምብጥ ወጣቶች ማዕከል ውስጥ ቢሮ ሰጥቶናል፡፡ ወጣት ማዕከሉ አዳራሽ ስላለው አዳራሹን ለድጋፍ መሰብሰቢያ ስራዎቻችን እንጠቀማለን» በማለት መንግሥት ለማኅበሩ ስለሚያደርጋቸው ድጋፎች ያስረዳሉ፡፡

ባህልና ወግን ከማስጠበቅ አንፃር እንዲሁ ማህበሩ ይሰራል፡፡ አቶ ምኅረት ይህንንም አብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ፣ በ2013 ዓ.ም 12 የማኅበሩ አባላት ከባህር ዳር ወደ ላሊበላ የ310 ኪሎ ሜትር የእግር ጉዞ ሲያደርጉ፣ በወቅቱ በአካባቢው ጦርነት ስለነበር ከሰላምና ደህንነት እንዲሁም ከባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤቶች ደብዳቤዎችን አግኝተው ጉዞ ስለማድረጋቸው ያስታውሳሉ፡፡

ድርጅቱ ስራዎቹን ሲያከናውን ስለሚያጋጥሙት ችግሮችም አቶ ምኅረት አመልክተዋል፡፡ «ማኅበሩ ስራውን በጀመረባቸው ዓመታት ከነበሩ ፈተናዎች መካከል አንዱ የአመለካከት ችግር ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች ‹ገንዘቡ ለትክክለኛው ዓላማ አይውልም› ብለው የማሰብ አዝማሚያ ይታይባቸው ነበር፤ ይህ ችግር አሁን የለም» ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል የነበረው የሰዎች አስተሳሰብ ተቀይሮ ማኅበሩ ለግለሰቦችና ለተቋማት የድጋፍ ጥያቄ ሲያቀርብ ሁሉም አቅሙ የፈቀደውን የገንዘብ፣ የአልባሳት፣ የቁሳቁስና የምግብ ድጋፍ ያደርጋል፤ ድርጅቶችም ወደ ማኅበሩ በመምጣት ድጋፍ እንደሚያደርግ አስታውቀዋል፡፡ በኑሮ ውድነትና በሌሎች ችግሮች ምክንያት አሁን ያለንበት ወቅት ብዙ ሰዎች ድጋፍ የሚፈልጉበት ጊዜ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳ ብዙ ሰዎችን ተደራሽ ማድረግ እየተቻለ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡ የቦታ ጥበትም ሌላው ችግር መሆኑን ጠቁመው፣ ችግሩን ለመፍታት ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ጋር በመነጋገር መፍትሄ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ችግር ፈቺ ተግባራት ላይ በመመስረት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ እነዚህ ወገኖች ከችግሮቻቸው ተላቅቀው በማኅበረሰብና ሀገር ግንባታ ሂደት የራሳቸውን አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ የማድረግ ዓላማን ይዞ የሚንቀሳቀሰው «ድንበር የለሽ» የበጎ አድራጎት ማኅበር፣ በዜጎች ሕይወት ላይ ዘላቂ ለውጥ ለመፍጠር እና ማኅበሩ የተደራጀ ተቋማዊ አቅም እንዲኖረው የሚያስችሉ የረጅም ጊዜ እቅዶች እንዳሉትም አቶ ምኅረት ይገልፃሉ፡፡

ዋናው የማኅበሩ እቅድ በግለሰቦችና በተቋማት ከመደገፍ ተላቅቆ ገቢ ማመንጨት የሚያስችል አቅም በመገንባት ለአባላትና ለሌሎች ወገኖች የሥራ እድል መፍጠር እና ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ግብረ ሰናይ ድርጅት መሆን ነው፡፡ በሌላ በኩል ለሰዎች እለታዊና ጊዜያዊ ድጋፎችን ከማድረግ ይልቅ ዘላቂ የሆኑና በሰዎች ህይወት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ሊፈጥሩ የሚችሉ ድጋፎችን በማድረግ ሰዎችን ከጥገኝነት አስተሳሰብ ማላቀቅ ላይ አተኩሮም ይሰራል፡፡ ሰው ድጋፍ ማድረግና መስጠት ያለበት ስለተረፈው ብቻ ሳይሆን መስጠት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በማመን አቅም በፈቀደ መጠን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት በጥልቀት ማስገንዘብም ሌላው የማኅበሩ እቅድ ነው፡፡

«ድንበር የለሽ» የበጎ አድራጎት ማኅበር፣ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ፣ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ያሏቸው የበጎ አድራጎት ተግባራትን ሲያከናውን በመቆየቱ ከበርካታ ተቋማት እውቅናዎችን አግኝቷል፡፡ ለድርጅቱ እውቅና ከሰጡ ተቋማት መካከል የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር፣ ዓድዋ የታሪክና ባህል ኅብረት፣ «ፓወር ቤዝ አምረፍ» እና ሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይጠቀሳሉ፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ለእግር ኳሳችን ትንሳዔ ትልቅ ርምጃ

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

ስለ ኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ወዳድነት መናገር ለቀባሪ የማርዳት ያህል ነው። ኢትዮጵያውያን ለእግር ኳስ ምን ያክል ዋጋ እንደከፈሉና እየከፈሉ እንዳሉ ከአፍሪካ ዋንጫ፣ እስከ ካፍ ምስረታ፣ ከካፍ ፕሬዚዳንትነት አሁን እስካለንበት የደጋፊ ስሜት ድረስ ያለውን መረዳት በቂ ነው። ከቀጠናዊ እስከ አህጉራዊ ብሎም እስከ ዓለም አቀፍ የሚደርሰው የደጋፊ ስሜት ኳስ ወዳድነታችንን ከማሳየቱ በላይ በእግር ኳሱ ላይ ያለንን ተስፋ የሚያሳይ ነው።

ታሪክ በእግር ኳሱ ላይ የኋሊት ቢምዘገዘግ በሆነ ዘመን ላይ ኢትዮጵያ የምትባልን ሀገር ያገኛል። እንደ ነጻነትና ስልጣኔ፣ ጥበብና ጀግንነት ሁሉ በአፍሪካ እግር ኳስም ቀደምት ታሪክ አለን። ዛሬ ላይ ያ ስም በነበር ተውጦ ድሮ ተብሎ የሚገለጽ ሆኗል። ካፍን ከመጀመር እስከ አፍሪካ ዋንጫን ማዘጋጀት ከፍ ሲልም ዋንጫ እስከ መብላት የደረሰ ድላችን ነፍስ አልዘራ ብሎ በመድረኩ ቀላዋጭ ካደረግን ብዙ ዓመታት አለፉ።

ከግብጽና ሱዳን ጋር ተባድነን የመጀመሪያውን የአፍሪካ ዋንጫ ለዓለም ያስተዋወቅን እኛ ነበርን። በማዘጋጀትና ዋንጫውንም በማስቀረት ስም ነበረን። ከዛ በኋላ በነበሩት የእግር ኳስ ታሪኮች ግን ተሳትፏችን እየቀነሰ ዋንጫ መብላት አይደለም ተሳትፎ ብርቅ እስኪሆንብን ድረስ ከታሪካችን ተለያየን።

ካፍ እና የአፍሪካ ዋንጫ ሲነሳ ስማቸው በቀዳሚነት ከሚታወስ የአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚዎቹ የሚለው ብኩርና ለኩራትና እንደ አፍሪካ ትልቅ ክብር የሚያሰጠን መሆኑ ባይካድም አሁን ላለንበት የኳስ ደረጃና የደጋፊ ስሜት ምላሽ መስጠት ግን አልቻለም። እንደ አጀማመራችንና አስተዋጽኦአችን ለምን በከፍታ እንዳልተጓዝን የተለያዩ ምክንያቶች ቢነሱም በሂደት እነዚህ ተቀርፈው ወደነበርንበት የከፍታ ማማ እንደምንመለስ ተስፋ እናደርጋለን።

ለዚህ ጽኑ ስሜታችን ተጠቃሽ በመሆን የሚነሳው ከአስር ዓመት በፊት ከሰላሳ አንድ ዓመት በኋላ ለአፍሪካ ዋንጫ ማለፋችንን ተከትሎ የነበረው የሕዝብ ስሜት አይረሳም። ያ ጊዜ ሕዝባችን ለኳስ ያለው ፍቅር እስከየት እንደሆነ ያየንበት ከመሆኑም በላይ የሀገር ፍቅር ስሜት የተንጸባረቀበትም ነበር። ሁሉንም ትተን በዛ ስሜት ብቻ ለኳስ ያለንን ስሜት መመዘን እንችላለን። ከዛ ከዛ በኋላም ስምንት ዓመት ጠብቀን ለ2021 የአፍሪካ ዋንጫ በቅተናል። ከዚህ በኋላ ባሉት ጊዜያቶች ለአፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ጉጉታችን ያልሰመረ ቢሆንም አሁንም ተስፋ ባለመቁረጥ ውስጥ እንገኛለን።

ይህን ተስፋ ከፍ የሚያደርግ ለተዳከመው እግር ኳሳችንም መነቃቃት የሚፈጥር አንድ ትልቅ ርምጃም በመንግስት በኩል ሰሞኑን ተወስዷል። ይህም በካፍ እና በፊፋ ፕሬዚዳንቶች ፊት በጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተነሳው የአፍሪካ ዋንጫን የእናዘጋጅ ጥያቄ ነው።

46ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ለማካሄድ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (ካፍ)ና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላቶቹ በጥቂት ቀናት ቆይታቸው ወቅት ስለኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ፍቅር ብዙ ተገንዝበው ተመልሰዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለልዑካኑ በታላቁ ቤተ-መንግስት የእራት ግብዣ ባደረጉበት ምሽትም ‹‹ኢትዮጵያ በ2029 የሚካሄደውን የአፍሪካ ዋንጫ የማዘጋጀት አቅም አላት› ሲሉ የፊፋና የካፍ አመራሮች ፊት የኢትዮጵያውያንን ስሜትና ፍላጎት አንጸባርቀዋል።

ይሄን ጥያቄ ተከትሎም የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙትሴፔ ለተደረገላቸው ደማቅ አቀባበልና መስተንግዶ ምስጋና በማቅረብ በኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነትና የትስስር እሴት መደነቃቸውን ገልጸው፣ በዚህም ኢትዮጵያ ቤታችን እንደሆነች እንዲሰማን ሆነናል ሲሉ ተናግረዋል። አያይዘውም የተነሳው የ2029 የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት መሻት ካፍ ከኮሚቴው ጋር እንደሚወያይበት አሳውቀዋል።

ስለነበረው ኢትዮጵያዊ ድባብ ንግግር ያደረጉት የፊፋው ፕሬዚዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ ‹የሰው ዘር መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ የኛም ሀገር ነች› ሲሉ ስሜታቸውን አጋርተዋል። በመርሀ ግብሩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለሁለቱ ፕሬዚዳንቶች የኢትዮጵያ እግር ኳስ ብሔራዊ ቡድን መለያን በስጦታነት አበርክተዋል። በተመሳሳይ የፊፋው ፕሬዚዳንት ጂያኒ ኢንፋንቲኖ 2029 የሚል ፊርማቸው ያረፈበትን ኳስ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አበርክተዋል።

**ብሔራዊ ቡድናችን በባዕድ ሀገርና ሜዳ ያለደጋፊ ሄዶ እንዲጫወት የሚገደድበት ደረጃውን የጠበቀ ስቴድየም ችግር አሁንም እንዳልተቀረፈ መሸሽግ አይቻልም**

በመንግስት በኩል የተነሳው የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት ጥያቄ ምክንያታዊ እንደነበር ብዙዎች ስሜታቸውን አንጸባርቀዋል። በተሰሩትና እየተሰሩ ባሉት ስታዲየሞችና መሰረተ ልማቶች የተደነቁት የካፍ ልዑካን ቡድኖች በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት አቅምና ሞራል እንዳላት ምስክርነታቸአውን ሰጥተዋል። ከጉባኤው መጠናቀቅ በኋላም መሰል አንቂና ሞራል ሰጪ ንግግሮች ከተሳታፊዎች ተደምጠዋል። የፊፋ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሞትሲፔን ጨምሮ ሌሎች አመራሮችም ጠቅላላ ጉባኤውን በተመለከተ ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጡ ይሄንኑ መስክረዋል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ እግር ኳስ ውስጥ ታሪካዊ ሚና እንዳላትና የካፍ መስራች አባል መሆኗን በተጨማሪም ለአፍሪካ ነጻነት ትልቅ ሚና የተጫወተች እንደሆነች ያነሱት የካፍ ፕሬዚዳንት፣ የአፍሪካ ዋንጫን የማስተናገድ ጥያቄዋም ወቅቱን የጠበቀና ትክክለኛ ውሳኔ እንደሆነ በመጠቆም በጎ ምላሽ እንደሚኖረው አመላክተዋል።

ሌሎች ተሳታፊ የቀድሞ ታዋቂ እግር ኳስ ተጫዋቾችም ባዩት ነገር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ‹‹ኢትዮጵያ የአፍሪካን ዋንጫ የማስተናገድ አቅም እንዳላት ተመልክቻለው›› ያለው የቀድሞ የሴኔጋል ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች አልሀጂ ዲዩፍ በእግር ኳሱ ላይ እየተሰሩ ያሉት ስራዎች ኢትዮጵያ ላነሳችው የአዘጋጅነት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በቂ ነው የሚል ሀሳቡን አጋርቷል። በእግር ኳሱ ላይ የነበረንንና ያለንን ጉልህ ሚና በመጥቀስም ሕዝቡ ለእግር ካሷ ያለውን ጽኑ ስሜት አድንቋል።

በተመሳሳይ የቀድሞ የናይጀሪያ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋች ተወዳጁ ጄይጄይ አካቻ ‹ኢትዮጵያ የትልቅ ስፖርት ሀገር በመሆኗ አፍሪካን በትልቅ የመወከል አቅም አላት› ያለ ሲሆን በተደረገላቸው አቀባበልም መደሰቱን ገልጿል። የሀገራችን የቀድሞ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾችም የዚህ ስሜት ተጋሪ በመሆን ሀሳባቸውን አካፍለዋል። ሳላሀዲን ሰይድ፣ ምን ያህል ተሾመና አዳነ ግርማ የካፍ መስራችነታችንን በማውሳት ለእግር ኳሱ እድገት እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በማድነቅ ተስፋ ሰጪነታቸውንም አያይዘው ተናግረዋል።

እኚህ የቀድሞ የብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት ጥያቄው ተገቢ እንደሆነ፣ እየተሰሩ ያሉ የስፖርት ማዘውተሪያዎችም ለዚህ ጉልበት እንደሚሆኑ በመግለጽ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽንን ማዘጋጀታችን ደግሞ የበለጠ ዋጋ የሚያሰጠን ነው ሲሉ ተደምጠዋል። ይሄን መሰሉን ሀሳብ ሌሎች አዲስ እና ነባር ተጫዋቾችም የሚጋሩት እንደሆነ መረዳት ቀላል ነው።

በነበረን ቁጭትና ለእግር ኳስ በከፈልነው ዋጋና ባለን ብርቱ ስሜት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደሀገር በስፖርቱ ዘርፍ የተሻሉ ነገሮችን በመስራት ላይ እንገኛለን። በካፍ ስታንዳርድ መሰረት ደረጃቸውን የጠበቁ ስታዲየሞችን መገንባት፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ማስፋፋት፣ የታዳጊ የስፖርት አካዳሚዎችንና ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ነገን ዛሬ ላይ እያለምን እንገኛለን።

ዝግጅታችንን ጨምሮ ያለው ነባራዊ ሁኔታና የአፍሪካ የኳስ ታሪካችን የአፍሪካ ዋንጫን ማዘጋጀት እንደምንችልና ከዚህም ላቅ ላለ ኃላፊነት መብቃት እንደምንችል ዋስትና መሆኑ በብዙዎች ዘንድ አመኔታን መፍጠሩ አጠራጣሪ አይሆንም። ለአፍሪካ የኳስ ትንሳኤ አድባር መሆናችን፣ የደጋፊዎቻችን የኳስ ፍቅር፣ በካፍ ላይ የነበረን አስተዋጽኦ ተደማምረው ጥያቄዎቻችን በጎ መልስ እንደሚያመጡ ይታመናል። ራስን እንዲህ ባለው የካፍና የፊፋ አመራር ልዑክ ማስተዋወቅ ዋጋው ትልቅ ነው። ታዋቂ ሰዎችን ጋብዞ ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ እንዲረዱ ማድረግ፣ በፊፋና በካፍ አመራሮች ዘንድ ማንነትን ማሳየት ትልቅ ተነሳሽነት እንደሆነ መረዳት ተገቢ ነው።

በዚህ ልክ ሌሎች እንዲረዱን መሆኑ ከኳስ ባሻገር እንደሀገር በርካታ ጥቅሞችን ይዞ የሚመጣ ነው። በእግር ኳሱ ረገድ ይዞት የሚመጣው መነቃቃት ዋነኛው ሲሆን ከዚህ ጋር አብረው የሚመጡ በርካታ በረከቶችም አሉ። ሌላ ሌላውን ትተን እንኳን በነበረው የብሔራዊ ስቴድየም ግንባታ የመስክ ጉብኝትና በልዑካን ቡድኑ የተሰጠን ገንቢ አስተያየት ቀላል አይደለም። በእግር ኳሱ መሰረተ ልማት ተስፋ ሰጪ ነገሮች እንዳሉ ከማሳየት ባለፈ ወደቀደመ ክብራችን ለመመለስ እያደረግነው ያለውን ተጋድሎ የሚያሳይም ነው። በእግር ኳሳችን ላይ በተለይም ደረጃውን የጠበቀ ስቴድየም ባለመኖሩ ብዙ ጥያቄዎች ይነሳሉ። እኚህ ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል በቅርብ ጊዜ እልባት እንደሚያገኙ የማይካድ ቢሆንም ወደፊት ከዚህ የተሻለ ሰርተን ከአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅነት ወደሌሎችም ታላላቅ መድረኮች አዘጋጅነት መሸጋገር እንችላለን።

ብሔራዊ ቡድናችን በባዕድ ሀገርና ሜዳ ያለደጋፊ ሄዶ እንዲጫወት የሚገደድበት ደረጃውን የጠበቀ ስቴድየም ችግር አሁንም እንዳልተቀረፈ መሸሸግ አይቻልም። ዛሬ ላይ የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት ጥያቄ ሲነሳም በበርካቶች ዘንድ እንደሚሳካ ስጋት አለ። የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት መነሳታችን ግን ባይሳካ እንኳን ይህን ጥያቄ በዘላቂነት ለመመለስ ይዞት የሚመጣው መልካም አጋጣሚ እንደሚኖር አርቆ ማሰብ ተገቢ ነው።

በታዋቂና በስመ ጥር ግለሰቦች የሀገርን ገጽታ ለሌላው ማኅበረሰብ ማስተዋወቅ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ይሉት አይነት ትርጉም ያለው ነው። የመጀመሪያው የልምድ ልውውጥ ነው። ቀጥሎ የሚመጣው የእግር ኳስ ደረጃችንን ማሳየትና በቀጣይ ለምናደርጋቸው ነገሮች በተጨባጭ ማሳየት ነው። ካፍ በኢትዮጵያ በነበረው ቆይታም ሁለቱም ግባቸውን መተዋል። አፍሪካ ዋንጫ ላይ መሳተፍ ብርቅ የሆነበት ትውልድ አፍሪካ ዋንጫን ሊያዘጋጅ ጥያቄ አቅርቦ መልስ በመጠባበቅ ላይ መገኘቱ በራሱ ትልቅ ትርጉም አለው።

እንዲህ አይነቱ ሁኔታ የነበሩንን በማስታወስ ቀጣይ ሂደታችንንም የሚያቀላጥፉልን ናቸው። ከዚህ ባለፈ አብሮ የሚነሳው ነገር ገጽታ ግንባታ ነው። አንድ ታዋቂ ሰው ከሀገራችን ወደሀገሩ ሲመለስ ብዙ ነገራችንን ለሌሎች በማጋራትና ዳግመኛ መመለስን በማሰብ ነው። ይሄ መሆኑ ከእግር ኳስ የእርስ በርስ ትስስር ጎን ለጎን እስከ ገጽታ ግንባታና የቱሪዝም ፍሰት ድረስ ባለው ደረጃ ተጠቃሚነታችንን የሚያረጋግጥ ነው። ሀገራች ኢትዮጵያ ያልተሰራባቸው ቢሰራባቸውም ተገቢውን ጥቅም ካላስገኙ ዘርፎች የቱሪስት መስህብ ተጠቃሽ ነው። እንዲህ አይነቱን አካሄድ ከማስተካከልና ትርፍ ከማምጣት አኳያ ሚናቸውም አብሮ የሚነሳ ነው።

የሀገራት የገቢ ምንጭ ኤክስፖርትን ከመሳሰሉ የኢኮኖሚ ዋልታ እኩል በገጽታ ግንባታ ጀምሮ በቱሪዝ ፍሰት የቀጠለ እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ እውነታ ነው። ለኳሱ እድል መስጠት ማለት ለብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻችን መልስ መስጠት ሆኖ ሊታይ የሚገባው ነው። እንደእግር ኳስና አትሌቲክስ ያሉ ብዙሀኑ የሚታደምባቸውና የሚመለከታቸው ጨዋታዎች ብዙ ትርፎች የሚገኙባቸው ላቅ ሲልም ለተሻለ ሀገረ ግንባታ መሰረት የሚጣልባቸውም ናቸው። ስለሆነም ወደኳሱ ማየት፣ ለእግር ኳሳችን ዋጋ መስጠት በዚህ ልክ ሊታይ የሚችል ይመስለኛል።

ከግብጽና ከሱዳን ጋር በመሆን ኳስን ለአፍሪካውያን ያስተዋወቀች፣ ካፍን የመሰረተች፣ የመራች፣ አፍሪካ ነጻነት ተምሳሌት የሆነች፣ የስልጣኔና የብኩርና ምድር ከተሳትፎ ልቃ የአፍሪካ ዋንጫን የምታዘጋጅበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። ወደቀደመ የከፍታ ምኩራቧ አዘንብላ የጸሀይ መውጫ ምስራቅነቷ ይቀጥላል። ሰላም መጥቶ፣ ፍቅር በዝቶ፣ እርቅ ወርዶ፣ አብሮነት ጎምርቶ፣ ኢትዮጵያዊነት ለምልሞ፣ ወንድማማችነት አብቦ፣ ሳቅ እና ትቅቅፍ በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ፈንጭተው ሁሉም ነገር መልካም የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል።

# ስፖርት




# ዋልያዎቹ በአዲስ አሰልጣኝ የቻን ማጣሪያን ይጀምራሉ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) ከሳምንት በፊት በ2025 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከጊኒ ጋር ያደረጉትን ሁለት ጨዋታ በሽንፈት ከደመደሙ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሌላ አህጉራዊ ተሳትፎ መልሰዋል። በሀገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾች የሚሳተፉበት የአፍሪካ ዋንጫ (ቻን) የማጣሪያ ውድድሮች በቅርቡ ሲከናወኑ ዋልያዎቹ በአዲስ አሰልጣኝ እንደሚመሩ የኢትዮጵያ እግር ካስ ፌዴሬሽን አሳውቋል።

ባለፈው አንድ ዓመት ገደማ ዋልያዎቹን ሲመሩ የቆዩት አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ተሰናብተው አሰልጣኝ መሳይ ተፈሪ ብሔራዊ ቡድኑን በጊዜያዊነት እንዲመሩ መወሰኑን ፌዴሬሽኑ ከትናንት በስቲያ አረጋግጧል።

ፌዴሬሽኑና አሠልጣኝ ገብረመድህን ያላቸው የአንድ ዓመት የኮንትራት ስምምነት የሚጠናቀቀው ከቀናት በኋላ ጥቅምት 22 ቀን 2017 ዓ.ም ቢሆንም የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ባደረገው ስብሠባ ላይ ከአሠልጣኙ ጋር መለያየቱ ታውቋል። በዚህም በምክትል አሠልጣኝነት ሲያገለግል የነበረውን አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ በዋና አሠልጣኝነት ጊዜያዊ ሆኖ ዋልያዎቹን እንዲመራ ውሳኔ ላይ ተደርሷል።

ፌዴሬሽኑ እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሰው የቻን የማጣሪያ ውድድር ላይ በዋናው ብሔራዊ ቡድን ውስጥ ከነበሩት ከሱራፌል ዳኛቸውና ከአቤል ማሞ በስተቀር ሁሉም ተጫዋቾች በቻን ውድድር ላይ የሚሳተፉ በመሆኑ ብሔራዊ ቡድኑ በምክትል አሠልጣኙ መመራት ይችላል በማለት ነው። ይህም የፌዴሬሽኑ ውሳኔ በቀጣይ ሌሎች አሠልጣኞችን ተረጋግቶ ለማየት ዕድል ይሰጣል ተብሎ ታምኖበታል።

በፌዴሬሽኑ አዲስ ኃላፊነት የተሠጠው አሠልጣኝ መሳይ ተፈሪ የአሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ረዳት በመሆን ላለፉት 12 ወራት ያገለገለ ሲሆን በቻን የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ከኤርትራ ጋር የሚደረገውን ጨዋታ ጨምሮ በሌሎች ማጣሪያዎችም ዋልያዎቹን ይመራል። ይህንንም ተከትሎ ለቻን ማጣሪያ ዝግጅት ከትናንት ጀምሮ እንዲሰባሰቡ ለ23 ተጫዋቾች ጥሪ አቅርቧል። የተጫዋቾቹ ጥሪ የኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ውድድርን ባማከለ መልኩ የተከናወነ በመሆኑም ሊጉ የማይቋረጥ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በቻን የመጀመሪያ ዙር የደርሶ መልስ ቅድመ ማጣሪያ ከኤርትራ ጋር መደልደሉ የሚታወስ ሲሆን ጨዋታው ጥቅምት 21 እና 24 በደቡብ ሱዳን ጁባ ብሔራዊ ስቴዲየም ይካሄዳል።

በዚህ የማጣሪያ ውድድር በመካከለኛውና ምስራቅ አፍሪካ (ሴካፋ) ዞን አስራ አንድ ሀገራት በቻን ተሳታፊ ለመሆን ይፋለማሉ። የኢትዮጵያና የኤርትራ የደርሶ መልስ ጨዋታ ድምር ውጤት አሸናፊም ከሱዳንና ታንዛኒያ አሸናፊ ጋር የሚገናኝ ይሆናል። በሌላኛው ምድብ ቡሩንዲና ሶማሊያ የተደለደሉ ሲሆን ሁለቱን የቅድመ ማጣሪያ ጨዋታዎች ማሸነፍ የቻለው ሀገር የተሻለ የእግር ካስ ደረጃ በመያዝ በቀጥታ በሁለተኛው ዙር ማጣሪያ የምትሳተፈው ዩጋንዳን ይገጥማል። ደቡብ ሱዳንና ኬንያ በሚገኙበት ምድብ አሸናፊ የሆነው ሀገር ደግሞ የጅቡቲና ርዋንዳ አሸናፊን ይገጥማል።

የ2027 የአፍሪካ ዋንጫን በጣምራ የሚያዘጋጁት ኬንያ፣ ዩጋንዳና ታንዛኒያ የ2025 የቻን ዋንጫን በተመሳሳይ በጣምራ ያስተናግዳሉ። በዋናው የአፍሪካ ዋንጫ በሌሎች ዓለማት ታላላቅ ሊጎች በሚጫወቱ ኮከቦች የተሸፈኑና በሀገር ውስጥ ሊጎች ብቻ የሚጫወቱ ተጫዋቾችን እድል ለመስጠት እኤአ ከ2009 ጀምሮ እየተካሄደ በሚካሄደው የቻን ዋንጫ ከሴካፋ ዞን አራት ሀገራት ተሳታፊ ይሆናሉ። በሌሎች ዞኖች የሚገኙት ግን ሦስት ሦስት ሀገራትን ብቻ የሚያሳትፉ ይሆናል። ይህም ካፍ ዝቅተኛ የእግር ኳስ ደረጃ ያለውን የሴካፋ ዞን ለማበረታታት የሚያደርገው ነው።



**አሰልጣኝ መሳይ ተፈሪ፣**

በሴካፋ ዞን ከሚገኙ ሀገራት ዩጋንዳ ከሰባት የቻን ውድድሮች በስድስቱ በመሳተፍ ቀዳሚ ስትሆን ርዋንዳ አራት ጊዜ፣ ኢትዮጵያና ሱዳን ደግሞ ሦስት ጊዜ የመሳተፍ ታሪክ አላቸው።

## ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ሌሎች ከተሞች ሊማሩበት የሚገባ የመዲናዋ ተሞክሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ባለፈው ዓመት በከተማና መሠረተ ልማት ለሙስና ተጋላጭ ያላቸውን አሠራሮችና ዘርፎች በሚመለከት ባደረገው የዳሰሳ ጥናት የመሬት ዘርፍ ለከፍተኛ ሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ አሠራሮች መኖራቸውን ይፋ አድርጎ ነበር። በኮሚሽኑ የቀረበው የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው የከተሞች ፕላን በአግባቡ አለመተግበር፣ ለልማት የሚውል መሬት ላልተፈለገ ዓላማ መዋል፣ ከካሳ ክፍያ ጋር የተገናኘ ማጭበርበር፣ ሀብትን ወደ ውጭ የማሸሽና የማሻገር፣ በትልልቅ ኮንትራክተሮች በፕሮጀክቶች ላይ የሚፈጸም ሙስና፣ ከሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ጋር የተያያዘ ሙስና፣ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ደርቦ መስጠት፣ ከመሬት መጠቀሚያ ዓላማ ውጪ ለሌላ ዓላማ ደርቦ መስጠት፣ ሕግን ያልተከተለ የይዞታ መብት መስጠትና የመሬት ወረራ፣ እንዲሁም ሕግን ያልተከተለ ምትክ ቦታ መስጠት የሚሉት ችግሮች በዋቢነት ቀርበዋል።

ይህንን በአግባቡ የተረዳው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሪፎርም ስራዎችን መስራት ከጀመረ ሰነባብቷል። ሰሞኑንም የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ፣ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ ፋንታ ደጀንና ሌሎች አመራሮች ከከንቲባ አዳነች አቤቤ ጋር በመሆን የቢሮው ሁለንተናዊ የሪፎርም ሥራዎች ያሉበትን ደረጃ ጎብኝተዋል። የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተም የቢሮው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ማብራሪያ ሰጥተዋቸዋል።

በወቅቱ የከተማው የመሬት ልማት አስተዳደር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች እንደገለፁት ቢሮው ባደረገው ሪፎርም አሠራሩን በማዘመን የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ አድርጓል። በዚህም የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መገንባት፣ ተቋማትን በኔትወርክ ማገናኘት፣ የሲስተም ልማትና የመረጃ ዲጅታላይዜሽን ሥራዎች ተከናውነዋል። የተቋሙ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሠራር በተደረገው ሪፎም አመርቂ ውጤት እንደተመዘገበባቸው አስረድተዋል።

ጉብኝቱን ተከትሎ ከንቲባ አዳች አቤቤ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ብልሹ አሠራርና የተገልጋይ እንግልት የተንሰራፋበት እና በርካታ ውጣ ውረዶች የነበሩበት ተቋም እንደነበር ተናግረዋል። አሁን ላይ ሁሉም የመሬት መረጃዎች ስካን ተደርገው ዲጂታላይዝ በሆነ መንገድ እንዲቀመጡ፣ አዳዲስ ፋይሎች አስርጎ ማስገባት እንዳይቻል፣መሬት አላግባብ የሚወስዱትን ለመቆጣጠር፣ የዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል። በሂደቱም በከተማ አስተዳደሩ ከ40 ሺህ በላይ የዘርፉን ተገልጋዮች ከነሙሉ መረጃዎቻቸው ዲጂታላይዝድ በሆነ መንገድ መመዝገባቸውንና መሬትን አላግባብ ሲጠቀሙ የነበሩ ነዋሪዎችም መያዛቸውን ከንቲባዋ ጠቁመዋል።

እንደከንቲባዋ ገለፃ በሪፎሙ የተዘረጋው ቴክኖሎጂ ከተማ አስተዳደሩ ያሉትን ሀብቶች በተገቢው እንዲያስተዳደር የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ሌብነትን ለማስቀረት እገዛው ላቅ ያለ ነው። የተጀመረው አሰራር ከዚህ በኋላ በመሬት ዙሪያ ለማታለል የሚደረግ ጥረትን ለመግታት፣ የሚጠፉ ፋይልም እንዳይኖርና ተገልጋይ መብቱ እንዲጠበቅለት ያስችላል። አሰራሩ ማንም ዜጋ ባለበት ሆኖ/ውጭ ሀገርም ቢሆን የመሬት ካርታ መረጃ የሚያገኝበት ሁኔታ የሚያመቻች እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በዚህ መንገድ እየተተገበረ ያለው ሪፎርም ውጤት ባለድርሻ አካላትና አመራሩ የፈጠሩት ቅንጅትና ለተግባራዊነቱ ያሳዩት ቁርጠኝነት መሆኑን ጠቁመዋል። በቢሮ የታዩ ለውጦች ልምድ ተቀምሮባቸው በሌሎች የከተማ አስተዳደሩ ቢሮዎችም ሊሰሩባቸው እንደሚገባም ከንቲባዋ አሳስበዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው በጉብኝቱ በቢሮው የመሬት መረጃ በአግባቡ ተመዝግቦ መያዙን ማየት መቻላቸውን ተናግረዋል። የተተገበረው ሪፎርም ለሌሎች ከተሞች ተሞክሮ እንደሚሆንና ለከተሞቻችን ከፍታ አንዱ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል። ቢሮው በቴክኖሎጂ የታገዘ አሠራር መዘርጋቱ ለአገልግሎት አሰጣጡ ምቹ መደላድል መፍጠር መቻሉንም አንስተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬትና ልማትና አስተዳደር ቢሮ የተቀናጀ መሬት አያያዝ ቡድን መሪ አቶ ፍፁም ኤልያስ የተደረገውን ለውጥ በተመለከተ እንደነገሩን የቢሮው ዲጂታላይዜሽን ስራ ሁለት ዋናዋና ክፍሎች አሉት። አንደኛው የማኅደር ዲጂታላይዜሽን ሲሆን የልዩ /ስፔሻል መረጃ ዲጂታላይዜሽን ሌላኛው ነው። እነዚህን ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ወደ አዲስ ቴክኖሎጂ የማስገባት ሥራዎች ተሰርተዋል። እንደከተማ አስተዳደር የመሬት ተቋም ትልቁ ሀብቱ ማኅደር በመሆኑ ይህንን ከሰዎች ንክኪና ጠፋ ከሚባልበትም ቦታ ለማውጣት ትልቅ ሥራ ተሠርቷል። በዚህም በ11ዱም ክፍለ ከተማ ከ670 ሺህ በላይ ስካን የተደረጉ ማኅደራት መረጃዎች በአንድ ቋት ገብተዋል። ቋቱ ውስጥ የገባ መረጃ ማንም የማያጠፋው፣ የማይሰርዘው፣ የማይደልዘው መሆኑንም ገልፀዋል።

እንደቡድን መሪው ገለፃ ልዩ መረጃዎች / ስፔሻል ዳታዎች ካርታዎችን የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህን መረጃዎች በዋናነት በአንድ ማዕከላዊ መሠረተ ካርታ ሥር /ሰርቨር የሚተዳደሩበትን ሁኔታ ያሚያመቻች ነው። በዚህም አዲስ አበባ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ መረጃዎችን በማደራጀትና አንድ ማዕከላዊ መሠረተ ካርታ /ቤዝ ማፕ ማደራጀት ችላለች። በዚሁ በልዩ መረጃዎች አማካኝነት የመሬት ባንክ፣ ካሳ፣ የመሬት ዝግጅትን የተመለከቱ መረጃዎች አብረው እንዲደራጁ ተደርጓል። ክፍት ቦታዎች ታውቀው ከመያዛቸው ባለፈ ለሚፈለገው ሥራ ለሚፈለገው ዓላማ እንዲውሉ ማድረግ መቻሉን አስረድተዋል።

ቢሮው የዘረጋው አሰራር የመሬት ወረራንም ሆነ ሌሎች ሕገወጥ ተግባራትን ለማስቆም ሁነኛ መፍትሄ መሆኑን የቡድን መሪው አስረድተዋል። ብዙ ጊዜ ባለቤት የሌላቸው ቦታዎች / ጫካዎች፣ ደኖች፣ ወንዝ ዳርቻዎች ባህሪያቸው ለመሬት ወረራ ተጋላጭ ናቸው። እነዚህን ቦታዎች በተመለከተም ለልማት የሚውሉትን በማልማት፤ ለልማት የማይበቁትን የመንግሥት እንደሆኑ ተለክተውና መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚቀመጡበት ሥርዓት ተዘርግቷል። ይህ በመዲናዋ የተሠራው የመሬት ዲጂታላይዜሽን ተግባር ሌሎች ከተሞች ሊማሩበት እንደሚገባ አቶ ፍፁም እምነታቸውን ገልፀዋል።